የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሰላሳ አንደኛ ዓመት ቁጥር ፷፫
አዲስ አበባ ነሐሴ ፮ ቀን ፪፻፲፯ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

31st Year No.63
ADDIS ABABA 12th August, 2025

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩፬፻፫፻፸፮/፪፻፲፯

የእንስሳት ጤና እና ደህንነት አዋጅ.....ገጽ ፲፱፻፺፰

Content

Proclamation No. 1376/2025

Animal Health and Welfare Proclamation

.....Page 19098

አዋጅ ቁጥር ፩፬፻፫፻፸፮/፪፻፲፯

የእንስሳት ጤና እና ደህንነት አዋጅ

በዓለም አቀፍ ደረጃ ተዓማኒነት ያለው የእንስሳት ጤና አገልግሎት በማስፈን ወጪ ገቢና ተሸጋጋሪ በሆኑ እንስሳት የእንስሳት ውጤቶች ተዋፅኦዎችና ቁሶች ዝውውር ላይ ወደ ሀገር ውስጥ ሊገቡ ወይም ወደ ሌላ ሀገር ሊዛመቱ የሚችሉ በሽታዎችን መከላከልና መቆጣጠር በማስፈለጉ፤

በሀገራችን የሚገኙ የእንስሳት በሽታዎችን በመከላከል፣ በመቆጣጠርና ደረጃ በደረጃ ጨርሶ በማጥፋት የሰዎችን ሕይወትና ጤንነት በእንስሳትና በእንስሳት ውጤቶችና ተዋፅኦዎች አማካኝነት ወደ ሰው እና ከሰው ወደ እንስሳት የሚተላለፉ በሽታዎችን ለመከላከል የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የእንስሳት፣ የእንስሳት ውጤቶችና ተዋጽኦዎች ጥራትና ደህንነት አስገዳጅ መስፈርት እየሆነ በመምጣቱ ሀገራችን ያላትን የገበያ ድርሻ ለማስጠበቅና አዳዲስ ገበያዎች ውስጥ ዘልቆ ለመግባት የእንስሳት ልየታ፣ ምዝገባና ክትትል ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

እንስሳት ለሰው ልጅ ከሚያበረክቱት አስተዋጽኦ በላይ እንደሰው ስሜት ያላቸውና መሰረታዊ ፍላጎት እንዲሟላላቸው የሚሹ ፍጡራን በመሆናቸው በተለያየ ጊዜና ሁኔታ የሚደርስባቸውን የደህንነት ችግር ማሻሻልና መቅረፍ በማስፈለጉ፤

PROCLAMATION NO. 1376/2025

A PROCLAMATION FOR ANIMAL HEALTH AND WELFARE

WHEREAS, it has become increasingly important to build an internationally reliable veterinary service delivery system that can prevent and control the entry or spread of animal diseases resulting from the export, import, and transit of animals, animal products, by-products, and controlled article;

WHEREAS, it is found necessary to establish a system for prevention and control of animal diseases, and ultimately to eradicate them progressively from our country and thereby protect human health and life from risks associated with foods of animal origin and zoonotic diseases;

WHEREAS, it is found critically important to establish animal identification, registration, and traceability systems for animals, animal products, and by-products and to access into new markets as the safety and quality of these commodities have become a compulsory requirement;

WHEREAS, beyond their contribution to human beings, animals have feelings and basic needs like humans and hence, it is necessary to improve and alleviate animal welfare challenges that they face in different contexts.

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹፻፩
Negarit Gazeta P.O.Box 80001

Scanned with MOBILE SCANNER

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፤፤

ክፍል አንድ
ጠቅላላ ድንጋጌ

፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የእንስሳት ጤና እና ደህንነት አዋጅ ቁጥር ፩፻፫፻፸፮/፪፻፲፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፤፤

፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩/ "እንስሳ" ማለት ሰውን ሳይጨምር ማናቸውም አከርካሪ አጥንት ያላቸው አጥቢዎች፣ አዕዋፍ፣ የውሃ ውስጥና የየብስ ላይ እንስሳት ሲሆኑ፣ ንብንና የሐር ትልን ጨምሮ ሌሎች አከርካሪ የሌላቸው እንስሳትንም ይጨምራል፣

፪/ "እንስሳት ጤና" ማለት የእንስሳት ሕክምና አገልግሎት መስጠትን፣ የእንስሳት በሽታ መከላከል መቆጣጠርና ማስገወድን፣ የበሽታ ቅኝትና ዳሰሳን፣ የላብራቶሪ አገልግሎት በእንስሳት ሕክምና የሕብረተሰብ ጤና ጥበቃን፣ የምርት ጥራትና ደህንነት ቁጥጥርን፣ የዝቪና ወሮ ምርት እና ቁጥጥር የሚደረግበት ቁስን ቁጥጥር፣ የእንስሳት መድሃኒት አጠቃቀምን እንዲሁም የእንስሳት ምዝገባ ልየታና ክትትል ሌሎች ተያያዥ ተግባራትን ያካትታል፣

፫/ "ባለቤት አልባ እንስሳ" ማለት ባለቤት የሌለው ወይም ከባለቤቱ ወይም ከጠባቂው ቁጥጥርና ክትትል ያመለጠና የወጣ ወይም ባለቤቱን ማረጋገጥ ሳይቻል የቀረ እንስሳ ነው፣

፬/ "የእንስሳት ውጤት" ማለት ያልተዘጋጀ ወይም እንደ ተመረተ ጥሬ የሆነ ወይም በከፊል የተዘጋጀ ሥጋን፣ ተረፈ ሥጋን፣ ወተትን፣ እንቁላልን፣ ማርን፣ ዓሣን እና ሌሎች ከእንስሳት የሚገኙ ውጤቶችን እና ተዋጽኦዎችን ያጠቃልላል፣

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

PART ONE
GENERAL

1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Animal Health and Welfare Proclamation No. 1376/2025"

2. Definitions

In this Proclamation unless the context otherwise requires:

1/ "Animal" means, any vertebrate including mammals, birds, aquatic and terrestrial animals; bees and silkworms and any invertebrate,; excluding human beings

2/ Animal Health" means the provision of veterinary medical services, prevention, control, and eradication of animal diseases; disease surveillance; provision of laboratory services; veterinary public health; quality and safety control of animal products; regulation of import and export commodities and controlled articles; regulation and use of veterinary drug; registration, identification, and traceability of animals, and includes other related activities;

3/ "Stray animal" means any animal which has no owner or has been found out of its owner's or custodian's normal care and confinement or for which ownership cannot be readily ascertained;

4/ "Animal product" includes raw or unprocessed or semi-processed meat and meat products, milk, egg, honey, fish, and other products and secondary products derived from animals;

Scanned with MOBILE SCANNER

፭/ "የእርድ እንስሳ" ማለት እንደሀገራችን ባህልና ልማድ ወይም የውጭ ሥጋ ተቀባይ ሀገራት ፍላጎት ለሰው ልጅ ምግብነት የሚውሉ አጥቢ እንስሳት፣ ዓሳ፣ ዶሮና ሌሎች አእዋፋትን ያካትታል፣

5/ "Slaughter animals" means those mammals, fish, chickens and other birds slaughtered for human consumption according to the culture and customs of our country or as per the requiments of importing countries;

፮/ "ሥጋ" ማለት ማንኛውም ለሰው ልጅ ምግብነት እንዲውል የታሰበ የእንስሳት አካል ሲሆን የሥጋ ተረፈ-ምርትን አያካትትም፣

6/ "Meat" means any portion of animals flesh, excluding meat by-products, which is intended for human consumption;

፯/ "ተረፈ-ሥጋ" ማለት ከዋናው ሥጋ በስተቀር ያሉ የእንስሳት እርድ ውጤቶች ሲሆኑ እንደ ምላስ፣ ልብ፣ ሳንባ፣ ጉበት፣ ኩላሊት፣ ጣፊያ፣ እንስል፣ ቆለጥ፣ ቁርዝ፣ ደም፣ አጥንት፣ የበሬ ጅራት፣ ፊርስ የወጣለት ጨጓራና አንጀት የመሳሰሉትን ይጨምራል፣

7/ "Meat by-product" means a product drived form slaughtered animals other than meat including but not limited to tongue, heart, lungs, liver, kidneys, spleen, brain, testicles, penis, blood, bone, ox tail, stomach and intestine free of their content;

፰/ "የሥጋ መርማሪ" ማለት በዘርፉ የሰለጠነ፣ የሙያ የብቃት ማረጋገጫ ያለው እና በግብርና ባለስልጣን በቂራ ወይም ድርጅት ውስጥ የተመደበ ሆኖ በተቀመጠለት መስፈርት መሠረት የስጋና የስጋ ተረፈ ምርትን ደህንነትና ጥራት የሚመረምር፣ የሚቆጣጠር እና የሚያረጋግጥ ባለሙያ ነው፣

8/ "Meat inspector" means a trained and certified professional who is assigned by the Agricultural Authority at abattoirs and establishments to control and inspect the production, safety and quality of meat and meat by-products, according to pre-set standards;

፱/ "በከፊል የተዘጋጀ" ማለት እንደ ተመረተ ጥሬ ሆኖ የተከፋፈለ፣ በንጥረ ነገር ያልበለጸገ፣ ያልደረቀ፣ ጨው ያልገባበት እና በሌሎች ተፈጥሯዊ ይዘቱን በማይለውጡ ተመሳሳይ ሂደቶች አልፎ የታሸገም ሆነ ያልታሸገ ያካተተ ነው፣

9/ 'Semi-processed" refers to packaged or unpackaged product that is prepared raw and is untreated with additives, undried, unsalted, or has not undergone other processes that alter its natural content;

፲/ "የእንስሳት ተረፈ ምርት" ማለት ቆዳ፣ ሌጦ ፣ ፀጉር፣ ላባ፣ ዝባድ፣ ቀንድ፣ ሰም፣ ሽሆና፣ አጥንት፣ ሞራና ከነዚህ የሚገኙትን የመኖ ግብዓትን እንዲሁም ሚኒስቴሩ ወደፊት ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም ሲባል የእንስሳት ተረፈ ምርት ብሎ የሚሰይማቸውን ሁሉ ይጨምራል፣

10/ "Animal by-product" means hide, skin, hair, feather, musk, horn, beeswax, hoof, bone, tallow, and animal feed inputs derived from these and includes also all other by-products designated as such by the Ministry for the purpose of this Proclamation;

፲፩/ "ምርት" ማለት እንስሳትን፣ የእንስሳት ውጤቶችንና ተዋጽዖችን፣ የእንስሳት ዘረመልን፣ ሥነ-ሕይወታዊ ቁስን፣ ባዮሎጂካል ውጤቶችን፣ የእንስሳት መኖን፣ በሽታ አምጪ ተህዋስ ያለበት ናሙናን ይጨምራል፣

11/ "Commodity" includes animals, animal products and secondary products derived from animals, animal genetic material, biological materials, biological products, animal feedstuffs, and pathological samples;

Scanned with MOBILE SCANNER

፲፪/ "ሥነ-ሕይወታዊ ቁስ" ማለት የሥነ-ሕይወት ሁደት ውጤት ሲሆን የሴት ወይም የወንድ ዘርን፣ ፅንስን፣ ሽልን፣ ዘረመልን፣ ዕድገት አፋጣኝ ወይም ማንኛውንም የሥነ ሕይወት ሁደት ውጤቶችን ወይም ሌሎች የእንስሳትን አካላዊ ሁደትና ምርታማነት ለመለወጥ የሚውሉ ግብዓቶችን ይጨምራል፤

12/ "Biological material" means any product of a biological process, including ova, semen, embryos, fetus, genetic material, hormones, or any other biological materials or other inputs used to alter the bodily functions or performance of an animal;

፲፫/ "የእንስሳት በሽታ" ማለት በማንኛውም በሽታ አምጪ ነገር የሚከሰት ሆኖ የእንስሳውን አካል ወይም ብልት ጤናማ ስራ እንዲታወክ ወይም እንዲገታ የሚያደርግ ነው፤

13/ "Animal disease" means an impairment or disturbance of the normal function of any organ or the body of any animal that is caused by any disease-causing agents;

፲፬/ "ዙኖሲስ" ማለት ከእንስሳት ወደ ሰው ወይም ከሰው ወደ እንስሳት የሚተላለፍ ማንኛውም በሽታ ነው፤

14/ "Zoonosis" means any animal disease or infection which is transmissible from animals to humans and vice versa;

፲፭/ "አዲስ ወይም እንደገና የተከሰተ የእንስሳት በሽታ" ማለት በሽታ አስተላላፊ ተህዋስያን በሚያደርጉት አዝጋሚና ድንገተኛ ለውጥ አዲስ በሽታ ሲፈጠር ወይም ቀደም ብሎ የሚታወቅ በሽታ ወይም በሽታ አስተላላፊ ተህዋስ ወደ አዲስ አካባቢና መንጋ ሲተላለፍ ወይም ጨርሶ የማይታወቅ አዲስ በሽታ ወይም በሽታ አምጪ ተህዋስ ለመጀመሪያ ጊዜ መኖሩ በምርመራ ሲረጋገጥ እና በሰው ወይም በእንስሳት ላይ ከፍተኛ የሆነ አሉታዊ ተፅዕኖ ሲያደርስ ነው፤

15/ "Emerging and re-emerging animal disease" means a new infection resulting from the evolution or change of an existing infectious organism, a known animal disease or infectious organism spreading to a new geographic area or population, or a previously unrecognized infectious organism or animal disease diagnosed for the first time and which has a significant impact on animal or public health;

፲፮/ "ሪፖርት መደረግ ያለበት የእንስሳት በሽታ" ማለት በማንኛውም ሰው መከሰቱ ሲጠረጠር ወይም በባለሙያ ሲረጋገጥ ለሚኒስቴሩ ወይም ለክልሉ የእንስሳት ጤና ተቋም ወይም ለዓለም አቀፉ የእንስሳት ጤና ድርጅት ሪፖርት መደረግ ያለበትና ሚኒስቴሩ ሪፖርት መደረግ ያለባቸው ብሎ ከሰየማቸው በሽታዎች መዘርዝር ውስጥ ያለ በሽታ ነው፤

16/ "Notifiable animal disease" means any animal disease which is declared to be a notifiable animal disease by the Ministry, as soon as it is detected or suspected by any person, or confirmed by an animal health professional and should be brought to the attention of the Ministry or Regional competent body or World Animal Health Organization;

፲፯/ "ቁጥጥር የሚደረግበት የእንስሳት በሽታ" ማለት አንድና ከአንድ በላይ የሆኑ የሳኒተሪ እርምጃዎችን በመውሰድ ቁጥጥር ሊደረግበት የሚገባውና ሚኒስቴሩ ቁጥጥር የሚደረግባቸው ብሎ ከሰየማቸው በሽታዎች ዝርዝር ውስጥ የተመደበ የእንስሳት በሽታ ነው፤

17/ "Controlled animal disease" means any notifiable animal disease which is deemed to be necessary to control through the application of one or more sanitary measures and is declared by the Ministry to be a controlled animal disease;

፲፰/ "ቁስ" ማለት ማንኛውም የህክምና መገልገያ፣ የቄራና የማቀነባበሪያ ድርጅት መገልገያ መሣሪያዎችን፣ ማጓጓዣ፣ ማሸጊያ፣ የላብራቶሪ እቃዎችንና መሣሪያዎችን የሚያጠቃልል ሲሆን ሌሎች መሣሪያዎችንና እቃዎችንም የሚያጠቃልል ነው፤

18/ "Article" means any medical equipment, abattoir and processing plant equipment, conveyance, packaging, laboratory items and equipment, and also includes other materials and items;

Scanned with MOBILE SCANNER

፲፱/ "ቁጥጥር የሚደረግበት ቁስ" ማለት ማንኛውም በሽታ አስተላላፊ መሆኑ የተጠረጠረ ወይም የተረጋገጠ እና በበሽታ አስተላላፊ ተህዋስ መበከሉ የተጠረጠረ ወይም የተረጋገጠ ሆኖ ወደ ሀገር ውስጥ ሲገባ፣ ሲሸጋገርና ወደ ውጭ ሲላክ ቁጥጥር የሚደረግበት ቁስ ነው፤

19/ "Controlled article" means any object which is either suspected or confirmed to be an infected article or a contaminated article that is controlled for the purposes of import into, transit through, or export from the territory of the country;

፳/ "የተበከለ ቁስ" ማለት ማንኳን ጨምሮ ማንኛውም በበሽታ አስተላላፊ ተህዋስ፣ ኬሚካል ወይም በሌሎች ጎጂ ነገሮች የተበከለ ወይም መበከሉ የተጠረጠረና በእነሱም አማካኝነት ለእንስሳት በሽታ፣ ከእንስሳት ወደ ሰው ለሚተላለፉ በሽታዎች ወይም ለሌሎች ጎጂ ሕመሞች፣ ለአካባቢ ብክለት መንስዔ የሆነ እና የተበከለ ተብሎ ሥልጣን ባለው አካል የተለየ ቁስ ነው፤

20/ "Contaminated article" means any material, including conveyance, which is contaminated or suspected to be contaminated with any infectious organism, chemical, or other harmful material by means of which an animal disease, zoonosis, or other form of illness or environmental contamination can be caused and which is declared to be a contaminated article Competent Authority;

፳፩/ "የእንስሳት በሽታ የቁጥጥር ፕሮግራም" ማለት ሚኒስቴሩ፣ ባለስልጣኑ እና የክልል የእንስሳት ጤና ተቋም በተመረጡ በሽታዎች ላይ በቅንጅት የሚያካሂዱት የመከላከልና የመቆጣጠር ፕሮግራም ነው፤

21/ "Animal disease control Program" means a program whereby by the Ministry, the Authority, and Regional Veterinary Body jointly excute for the prevention and control of certain notifiable animal diseases;

፳፪/ "የእንስሳት ደህንነት" ማለት እንስሳት ጤንነታቸው እና አመጋገባቸው ተጠብቆ፣ የተፈጥሮ ባህርያቸውን መግለፅ በሚችሉበት ሁኔታ ሆነው፣ ከስቃይ፣ ከሀሞም፣ ከፍርሃትና ከሮሮንቀት ተጠብቀው የሚያዙበት ሥርዓት ነው፤

22/ "Animal welfare" means a system in which an animal is kept healthy, comfortable, well nourished, safe, able to express innate behaviours, and not suffering from unpleasant states such as pain, fear, and distress;

፳፫/ "የሥነ-ሕይወታዊ ደህንነት" ማለት የእንስሳት በሽታ፣ በሽታ አምጭ ተህዋሲያን ወደ እንስሳት መንጋ እንዳይገቡ እንዳይሰራፉ ለመከላከል የሚንደፉና የሚተገበሩ ተግባራት ናቸው፤

23/ "Biosecurity" means a set of measures designed and implement to prevent the introduction, and spread of animal diseases, infectious agent to an animal population;

፳፬/ "የእንስሳት ክትትል" ማለት እንስሳትን በሕይወት ዘመናቸው በመንጋ ወይም በተናጠል የመከታተል ሂደት ነው፤

24/ "Animal traceability" means the ability to follow an animal or group of animals during all stages of their life;

፳፭/ "የእንስሳት ውጤት ክትትል" ማለት የእንስሳት ውጤትን ከምርት ሂደት ጀምሮ ተፈጥሯዊ ይዘቱን ሳይቀይር ለተጠቃሚው እስኪቀርብ ድረስ የሚደረግ የመከታተል ሂደት ነው፤

25/ "Animal product traceability" means the ability to follow an animal product from the point of production to provision to the consumer without altering its natural content;

Scanned with MOBILE SCANNER

፳፮/ "የእንስሳት መለያ ምልክት" ማለት በሚኒስቴሩ የተመዘገበ እና እውቅና የተሰጠው ማንኛውም እንስሳትን ለመለየት የሚያገለግል ምልክት ነው፤

፳፯/ "የተመዘገበ እንስሳ" ማለት መለያ ምልክት ተደርጎበት መረጃው በብሔራዊ የእንስሳት መረጃ ቋት ውስጥ የሚገኝ እንስሳ ነው፤

፳፰ "የእንስሳት መሰብሰብ" ማለት ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ከሆኑ ተቋማት ለሽያጭ፣ ለትርዒት ወይም ለኤግዚቢሽን ወይም ለመጓጓዝ ወይም ለምርመራ ወይም ለመሳሰሉት ተግባራት ለማዋል የሚደረግ የእንስሳት ስብስብ ነው፤

፳፱/ "ስልጣን ያለው አካል" ማለት ሚኒስቴሩ ወይም ባለስልጣኑ ወይም የእንስሳት ጤና ጥበቃ ተግባራትን እንዲያከናውን እና እንዲቆጣጠር፣ እንዲሁም የእንስሳትን ደህንነት እና በእንስሳት ሕክምና የህብረተሰብ ጤና ጥበቃ ተግባራትን እንዲያከናውን የተወከለ የክልል የእንስሳት ጤና ተቋም ነው፤

፴/ "ዋና የእንስሳት ጤና ኦፊሰር" ማለት በዋናነት የእንስሳት ጤና አገልግሎትን በመላው ሀገሪቱ ለመቆጣጠር በሚኒስቴሩ የተሰየመ የእንስሳት ጤና ኃላፊ ነው፤

፴፩/ "የእንስሳት ጤና ባለሙያ" ማለት ተገቢውን ትምህርት የወሰደ እና የእንሳሰት ጤና አግልግሎት ለመስጠት የተፈቀደለት ባለሙያ ነው፤

፴፪/ "የእንስሳት ጤና ተቆጣጣሪ" ማለት ሥልጣን ባለው አካል ውስጥ ተቀጣሪ የሆነ ወይም የተወከለ በዚህ አዋጅ ሥር የተቀመጡ የቁጥጥር ተግባራትን እንዲያከናውን ኃላፊነት የተሰጠው የእንስሳት ጤና ባለሙያ ነው፤

፴፫/ "የክልል ዋና የእንስሳት ጤና ዳይሬክተር" ማለት በዋናነት የእንስሳት ጤና አገልግሎትን በበላይነት የሚመራ በክልል የእንስሳት ጤና ተቋም በኃላፊነት የተሰየመ እና የክልሉ የእንስሳት ጤና መረጃን በተመለከተ ከፌደራል ዋና የእንስሳት ጤና ኦፊሰር ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት የሚያደርግ የእንስሳት ሀኪም ነው፤

26/ "Animal identification mark" means any mark recognized and registered by the Ministry to be placed on any animal for identification purposes;

27/ "Registered animal" means an identified animal which has been recorded in the national animal identification database;

28/ ''Animal gathering'' means an occasion at which animals are brought together from two or more establishments, for the purposes of a sale, show or exhibition, onward consignment, inspection, or any other similar purpose;

29/ "Competent Authority" means the Ministry or the Authority or delegated Regional Veterinary Body that is responsible for executing and controlling animal health, animal welfare, and veterinary public health activities;

30/ "Chief Veterinary Officer" means the principal veterinarian designated by the Ministry to supervise the veterinary Services in the whole territory of Ethiopia;

31/ "Animal health officer" means a professional with appropriate veterinary education who is authorized to deliver veterinary services;

32/ "Veterinary Inspector" means an animal health professional employed or delegated by the competent authority to perform regulatory activities stipulated under this proclamation;

33/ "Regional Veterinary Director" means a veterinarian designated by a Regional veterinary body to primarly lead the veterinary Services in the region and responsible for directly communicating with the Chief Veterinary Officer of the country;

Scanned with MOBILE SCANNER

፴፬/ "የክልል እንስሳት ጤና ተቋም" ማለት በክልል የእንስሳት ጤናን፣ ደህንነትን እና በእንስሳት ህክምና የህብረተሰብ ጤና አገልግሎትን የመስጠትና የመቆጣጠር ኃላፊነት ያለበት ተቋም ነው፣

34/ "Regional Veterinary Body" means a regional institution responsible for the delivery and regulation of animal health, welfare, and veterinary public health services;

፴፭/ "ግቢ" ማለት ማንኛውም በግልፅ የተለየ መሬት፣ ሕንፃ፣ ወደብ ወይም የታጠረ አካባቢ ሲሆን ከታ ገጠም ያልሆኑ ነገር ግን በአንድ ባለቤት ሥር የሆኑ ቦታዎችን ይጨምራል፣

35/ "Premises" means any defined area of land, building, structure, harbor or fenced enclosure including any disjoined land holding under the same ownership;

፴፮/ "የተመዘገበ ግቢ" ማለት እንስሳት የሚቆዩበት ቦታ ሆኖ በውስጡ ያሉ እንስሳትን ለመመዝገብና ለመለየት ሲባል በባለቤቱ ስም የምዝገባ ቁጥር የተሰጠው ግቢ ነው፣

36/ "Registered premises" means a place where animals are kept for the purposes of registration and identification, and whose owner has been allocated a registration number;

፴፯/ "ኮምፓርትመንት" ማለት በአንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆነ ቅጥር ግቢ ውስጥ የጋራ በሆነ ሥነ-ሕይወታዊ ደህንነት ሥርዓት ተጠብቀው ለተወሰኑ በሽታዎች በተመሳሳይ ይዞታ ላይ ያሉ ወይም ለዓለም አቀፍ ንግድ ሲባል በሽታዎችን ለመቆጣጠር የሚያስችሉ የቅኝት፣ የመከላከልና ሥነ-ሕይወታዊ ደህንነት እርምጃዎች የሚወሰድበት የእንስሳት ንዑስ ስብስብ ነው፣

37/ "compartment" means an animal subpopulation contained in one or more establishments under a common biosecurity management system with a distinct health status with respect to specific disease or diseases for which required surveillance, control, and biosecurity measures have been applied for the purpose of international trade;

፴፰/ "የሳኒተሪ እርምጃ" ማለት ለእንስሳት ወይም ለሰው ጤና እና ሕይወት ስጋት የሆኑ የበሽታ መንስኤዎች ሀገር ውስጥ እንዳይከሰቱ እንዲሁም ወደ ሀገር እንዳይገቡና እንዳይሰራጩ ለመቆጣጠርና ለመከላከል የሚተገበር እርምጃ ነው፣

38/ "Sanitary measure" means a measure destined to protect animal or human health or life from risks arising from the occurrence, entry, establishment, and spread of disease within the territory of the country;

፴፱/ "ሰብዓዊ አወጋገድ" ማለት እንስሳትን ስቃይ በሚቀንስ እና ርህራሄ በተሞላበት መንገድ ሕይወታቸው እንዲያልፍ ማድረግ ነው ፣

39/ ''Humane killing'' means the act of inducing death using a method with minimum pain and suffering, and is carried out with compassion to the animal;

፵/ "የማቆያ ስፍራ" ማለት እንስሳት በጊዜያዊነት የሚቆዩበት ቦታ ነው፣

40/ ''Holding ground'' means any establishment in which animals are held on a temporary basis;

፵፩/ "ኳራንቲን" ማለት እንስሳትን እና የእንስሳት ውጤቶችን ለተወሰነ ጊዜ ለይቶ በማቆየት ከሌሎች እንስሳት እና የእንስሳት ውጤቶች ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ እንዳይገናኙ በማድረግ እና ጤንነታቸውን እና ደህንነታቸውን በመከታተል እንደ-አስፈላጊነቱም ሕክምናና ምርመራ የሚሰጥበት አገልግሎት ነው፣

41/ "Quarantine" means a sanitary action under which animals and animal products are maintained in isolation for the specifeied period of time under supervison, with no direct or indirect contact with other animals and animal products, and if necessary, tested and treated;

Scanned with MOBILE SCANNER

፵፪/ "የኳራንቲን ጣቢያ" ማለት ለእንስሳት የኳራቲን አገልግሎት የሚሰጥበት የማቆያ ቦታ ነው፤

42/ "Quarantine station" means an establishment where animals are kept for the purpose of quarantine service;

፵፫/ "ማቀነባበሪያ ድርጅት" ማለት የእንስሳት ውጤቶች እና ተረፈ ምርትን ተፈጥሯዊ ይዘቱን ሳይለውጥ ለምግብነት ወይም ለሌላ አገልግሎት እንዲውሉ የሚያዘጋጅ ተቋም ነው፤ ይህም የእንስሳት ውጤትና የእንስሳት ተረፈ-ምርት ማከማቻ እና የማጓጓዣ አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን ያካትታል፤

43/ "Processing plant" means an institution that prepares animal products and by-products for food or other use without altering their natural composition. This includes animal product and by-product storage and transportation service providers;

፵፬/ "ማምረቻ ድርጅት" ማለት የእንስሳት ግብዓት ወይም ምርት የሚመረትባቸው ተቋማት ወይም የእርባታ ድርጅቶች ማለት ሲሆን እነዚህም የቁም እንስሳት፣ የስጋ እና የስጋ ተረፈ-ምርቶች፣ የዶሮ፣ የወተት፣ የማር፣ የአሣ እና ሌሎችንም የሚያካትት ሆኖ እንደ-አስፈላጊነቱ የማቆየት እና የማሸግ ስራ ተፈጥሯዊ ይዘቱን ሳይቀይር የሚከናወንበት ነው፤

44/ "Production establishment" means institutions or farms where animal inputs or products are produced, including livestock, meat and meat by-products, poultry, dairy, honey, fish, and others, as deemed necessary, where preserving and packaging are carried out without altering the natural content of the products;

፵፭/ "የዓለም አቀፍ የእንስሳት ጤና ድርጅት" ማለት በዓለም ዙሪያ የእንስሳት ጤናን እና ደህንነትን ለማሻሻል ኃላፊነት ያላቸው ሀገራት ተሰማምተው ያቋቋሙት ድርጅት ነው፤

45/ "World Organization for Animal Health" means an intergovernmental organization responsible for improving animal health and welfare worldwide;

፵፮/ "ቄራ" ማለት በሚመለከተው አካል የተመዘገበ እና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ሆኖ ለሰው ምግብነት የሚውሉ እንስሳት ጤንነታቸው ተመርምሮ የሚታረዱበት ሥጋ እና የሥጋ ተረፈ-ምርቱ የሚዘጋጅበት ድርጅት ነው፤

46/ "Abattoir" means; an establishment registered and certified by a competent authority, where animals slaughtered intended for human consumption are inspected for the health status, and where meat and meat by-product are prepared;

፵፯/ "ተሻጋሪ" ማለት እንስሳት፣ የእንስሳት ውጤት፣ ተዋጽኦ፣ ሌሎች ምርቶች እና ቁጥጥር የሚደረግበት ቁስ በመግቢያ በር በኩል ወደ ሀገር ውስጥ ከገቡ በኋላ የኢትዮጵያን ግዛት አልፈው ወደ ሌላ ሀገር የሚተላለፉበት ሂደት ነው፤

47/ "Transit" means the conveyance of an animal, animal product, secondary products derived from animals, other commodities, and controlled article that has been imported through a port of entry and in transit through the territory of Ethiopia to another country;

፵፰/ "ኮዴክስ አሊመንታሪየስ" ማለት ለሰው ምግብነት የሚውሉ የእንስሳትና የዕፅዋት ውጤቶችን ጥራትና ደህንነት ለማረጋገጥ በተባበሩት መንግሥታት የኮዴክስ አሊመንታሪየስ ኮሚሽን ተዘጋጅተው የሚወጡ በዓለም አቀፍ ደረጃ ስምምነት የተደረሰባቸውና የፀደቁ ደረጃዎች ናቸው፤

48/ "Codex Alimentarius" means the set of internationally agreed and approved standards, prepared and published by the Codex Alimentarius Commission of the United Nations, to ensure the safety and quality of foods of animal and plant origin destined for human consumption;

Scanned with MOBILE SCANNER

፵፱/ "ዓለም አቀፍ የእንስሳት ጤና ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት" ማለት በየብስ ወይም በውሃ እንስሳት ጤና ኮድ መሠረት የእንስሳውንና የምርቱን ዓይነትና በተቀባይ ሀገር ፍላጎት መሠረት ወደ ውጪ የሚላኩ ምርቶች የሚያሟሏቸውን መስፈርቶች በመጥቀስ የሚሰጥ ዓለም አቀፍ የምስክር ወረቀት ነው፤

49/ "International veterinary certificate" means an international certificate issued in conformity with the provisions of the Terrestrial and Aquatic Animal Health Codes, describing the necessary requirements to be fulfilled for export commodities in accordance with the sanitary requirement of the importing countries;

፶/ "የሳኒተሪ ማንዴት ውል" ማለት ስልጣን ባለው አካል እና በውል ተቀባይ የእንስሳት ጤና ባለሙያ ወይም ተቋም መካከል የተወሰኑና በግልፅ የተቀመጡ ተግባራትን በውል ሰጪው ስም ለመፈፀም የሚደረግ ስምምነት ነው፤

50/ "Sanitary mandate contract" means an agreement made between the competent authority and animal health professional or institution for the purpose of delegating certain defined functions to perform on behalf of the competent authority;

፶፩/ "የየብስ ወይም የውሃ ውስጥ እንስሳት ኮድ" ማለት ዓለም አቀፍ የእንስሳት ጤና ድርጅት ያወጣቸው የየብስና የውሃ ውስጥ እንስሳት ጤና ደረጃዎች ናቸው፤

51/ "Terrestrial or Aquatic Animal Code" means the terrestrial or aquatic animal health standard set by the World Organisation for Animal Health;

፶፪/ "የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት" ማለት ቁጥጥር የሚያስፈልጋቸው እንስሳትን፣ የእንስሳት፣ ውጤትን እና ተዋጽኦን ለማምረት፣ ወደ ገበያ ለማቅረብ፣ ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት ወይም ወደ ውጭ አገር ለመላክ መስፈርቶች መሟላታቸውን በባለስልጣኑ ተረጋግጦ የሚሰጥ ሕጋዊ የምዝገባ ሰነድ ነው፤

52/ "Certificate of Competence" means a legal certificate issued, to those who wish to engage in the production, marketing, import, or export of regulated animal, animal products, and –secondary products derived from animals, by the Authority upon fulfillment of the requirements;

፶፫/ "ሰው" ማለት በተፈጥሮ ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

53/ "Person" means a natural or juridical person;

፶፬/ "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 47 መሠረት የተካተተ ማንኛውም ክልል ማለት ሲሆን የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደርንም ይጨምራል፤

54/ "Region" means any of the Regional States specified under Article 47 of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and includes the Addis Ababa City and Dire Dawa City Administrations;

፶፭/ "ባለስልጣን" ማለት የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን ነው፤

55/"Authority" means Ethiopian Agricultural Authority;

፶፮/ "ሚኒስቴር" ማለት የግብርና ሚኒስቴር ነው፤

56/ "Ministry" means the Ministry of Agriculture;

፶፯/ ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ጾታ ይጨምራል።

57/ Any expressions in the masculine gender include the feminine.

Scanned with MOBILE SCANNER

፫. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ አዋጅ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የግዛት ወሰን ውስጥ በእንስሳት ጤና እና ደህንነት፣ ምርቶች እና ቁጥጥር የሚደረግበት ቁስ ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

ክፍል ሁለት

ስለአገልግሎት አሰጣጥ እና ስለእንስሳት ጤና ቦርድ

፬. የግል የእንስሳት ጤና አገልግሎት ስለመስጠት

ማንኛውም ሰው ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መስፈርት መሠረት የእንስሳት ጤና አገልግሎት መስጫ ጣቢያ፣ ማዕከል ወይም ተቋም ማቋቋም ይችላል።

፭. የእንስሳት ጤና ቦርድ

የእንስሳት ሐኪም እና ሌሎች የእንስሳት ጤና ባለሙያዎችን ለማብቃት እና ለመቆጣጠር በሚኒስትሩ አስተባባሪነት ከመንግስትና ከግል የዘርፉ ባለድርሻ አካላት አባል የሆኑበት የእንስሳት ጤና ቦርድ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል። የቦርዱ አባላት አወቃቀር፣ ሥልጣን እና ተግባሩን በተመለከተ ይህን አዋጅ ተከትሎ በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣው ደንብ ላይ የሚገለፅ ይሆናል።

ክፍል ሦስት

ሃገር አቀፍ የእንስሳት በሽታዎችን መከላከልና መቆጣጠር

፮. ሪፖርት መደረግ ያለበት አዲስ ወይም እንደገና የተከሰተ በሽታ የማሳወቅ ግዴታ

፩/ ማንኛውም የእንስሳት ባለቤት በሽታ መከሰቱን ሲጠረጥር ይህንኑ በአስቸኳይ በአቅራቢያው ለሚገኝ የእንስሳት ጤና ባለሙያ ወይም የአካባቢ መስተዳደር የማሳወቅ ግዴታ አለበት፣

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (፩) መሠረት ሪፖርት የተደረገለት የእንስሳት ጤና ባለሙያ ወይም የአካባቢ መስተዳደር በአካባቢው ሪፖርት መደረግ ያለበት አዲስ ወይም እንደገና የተከሰተ የእንስሳት በሽታ መከሰቱን መረጃ ሲደርሰው ወይም ሲጠረጥር

3. Scope of Application

This Proclamation shall be applicable to Animal health, welfare, commodites and controlled articles, within the territory of the Federal Democratic Republic of Ethiopia.

PART TWO

SERVICES DELIVERY AND VETERNIARY BOARD

4. Private Animal Health Services Delivery

Any person may establish an animal health station, center, or institution upon the fulfillment of the necessary requirements set by the Ministry.

5. Veterinary Board

A Veterinary Board, consisting representatives from both public and private sector stakeholders in the field, is hereby established by this Proclamation under the over all coordination of the Minister, for the purpose of regulating and certifying veterinarians and veterinary para professionals. The composition, powers, and responsibilities of the Board shall be detailed in a Regulation to be issued by the Council of Ministers pursuant to this Proclamation.

PART THREE

NATIONAL PREVENTION AND CONTROL OF ANIMAL DISEASES

6. Duty to Report Notifiable and Emerging and Re-Emerging Animal Diseases

1/ In the event that any animal owner suspects the occurrence of animal disease he shall immediately report the occurrance to the nearest animal health professional or local Administrative Office.

2/ Any Animal health professional or local administrative office who receives a report pursuant to Sub-Article (1) of this Article, or suspects the occurrence of a notifiable or an emerging or re-emerging animal disease shall report such

Scanned with MOBILE SCANNER

ይህንኑ ከ፲፪ ሰዓት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ በአቅራቢያው ለሚገኝ የእንስሳት ጤና ተቋም ማሳወቅ ይኖርበታል::

ፒ/ ሪፖርት መደረግ ያለበት ወይም አዲስ ወይም እንደገና የተከሰተ የእንስሳት በሽታ ለመከሰቱ ሪፖርት የተደረገለት በአቅራቢያው የሚገኝ የእንስሳት ጤና ተቋም በ፲፪ ሰዓት ውስጥ ሪፖርቱን ለክልሉ የእንስሳት ጤና ተቋም ማሳወቅ ይኖርበታል።

፬/ የክልሉ የእንስሳት ጤና ተቋም የደረሰውን የበሽታ ሪፖርት በ፲፪ ሰዓታት ውስጥ ለሃገራቱ ዋና የእንስሳት ጤና ኦፊሰር ማሳወቅ አለበት።

፭/ የሚኒስቴሩ ዋና የእንስሳት ጤና ኦፊሰር መከሰቱ የተጠረጠረውን ወይም የተረጋገጠውን ሪፖርት መደረግ ያለበት ወይም አዲስ ወይም እንደገና የተከሰተ የእንስሳት በሽታ የዓለም አቀፍ የእንስሳት ጤና ድርጅት በሚያዘው መመሪያ መሠረት ለዚሁ ድርጅት ሪፖርት ማድረግ አለበት።

፮/ የሚኒስቴሩ ዋና የእንስሳት ጤና ኦፊሰር መከሰቱ የተጠረጠረውን ወይም የተረጋገጠውን ሪፖርት መደረግ ያለበት ወይም አዲስ ወይም እንደገና የተከሰተ በሽታን በ፳፬ ሰዓት ውስጥ ለብሔራዊ ሳኒተሪ የመረጃና የሪፖርት ማሳወቂያ ኮሚቴ ማሳወቅ አለበት።

፯/ በሌሎች ሕጎች ከተፈቀደለት ሰው በስተቀር በእንስሳት በሽታ ዙሪያ ጥናት እና ምርምር የሚያካሂድ ሰው ግኝቱን ለሶስተኛ ወገን ይፋ ከማድረጉ በፊት ከሚኒስቴሩ ፈቃድ ማግኘት አለበት።

፰/ በዚህ አንቀጽ ሪፖርት መደረግ ያለበት ወይም አዲስ ወይም እንደገና የተከሰተ የእንስሳት በሽታ ሚኒስቴሩ በሚዘረጋው የበሽታ ማሳወቂያ የአሰራር ሥርዓት መሠረት ይከናወናል።

፯. <u>የእንስሳት በሽታ ቅኝት እና አሰሳ</u>

፩/ ሥልጣን ያለው አካል በየደረጃው ያሉ የመንግሥትና በግል የተመዘገቡ ሐኪሞችና ሌሎች የእንስሳት ጤና ባለሙያዎችን በመጠቀም ሪፖርት መደረግ ባለባቸውና አዲስ ወይም እንደገና የተከሰቱ በሽታዎች ላይ መረጃ ይሰበስባል፣ ያጠናቅራል፣ ይተነትናል፣ ያሰራጫል።

occurrence to the nearest veterinary authority no longer than 12 hours.

3/ The nearest veterinary authority receiving the report of a suspected notifiable or emerging or re-emerging animal disease shall forward such report to the Regional Veterinary Authority within 12 hours of receipt of such report.

4/ The Regional Veterinary Authority shall forward such report to the Country's Chief Veterinary Officer within 12 hours of receipt of such report.

5/ The Chief Veterinary Officer of the Ministry shall report suspected and confirmed occurrences of notifiable or emerging or re-emerging animal diseases to the World Animal Health Organization according to the organization's prescribed procedures.

6/ The Chief Veterinary Officer of the Ministry shall report to National Sanitary Enquiry Committee of any suspected or confirmed occurrence of a notifiable animal disease or an emerging or re-emerging animal disease within 24 hours.

7/ Except for a person authorized by other laws, any person shall get permission from the Ministry prior to publicizing his research findings on animal diseases.

8/ A notifiable or an emerging or re-emerging animal disease to be reported under this Aticle shall be carried out in accordance with disease notification system established by the Ministry.

7. <u>Animal Disease Surveillance and Survey</u>

1/ The Competent Authority by using both public and private registered veterinarians and veterinary para-professionals shall collect, record, analyze, and disseminate data, on notifiable or emerging, or re-emerging animal disease occurrences.

Scanned with MOBILE SCANNER

ፎ/ ሪፖርት መደረግ ያለበት ወይም አዲስ ወይም እንደገና የተከሰተ በሽታ መከሰቱን ሲጠረጠር ሚኒስቴሩ፣ ባለስልጣኑና የክልል የእንስሳት ጤና ተቋም በመተባበር የበሽታ አሰሳና የስርጭት መጠን እና ክስተት ላይ ክትትል ያደርጋሉ።

2/ In the event of the suspected occurrence of any notifiable, or emerging or re-emerging animal disease; the Ministry, the Authority,and theRegionalVeterinary Body shall collaborate to conduct surveillance and monitor the prevalence and incidence of these diseases.

ፐ/ ሪፖርት መደረግ ያለበት ወይም አዲስ ወይም እንደገና የተከሰተ በሽታ በተመለከተ የሚሰበሰብ ማንኛውም መረጃ በአግባቡና በጊዜ መጠናቀርና መመዝገብ ያለበት ሲሆን ለዋናው የእንስሳት ጤና ኦፊሰር መቅረብ ይኖርበታል።

3/ All data collected on notifiable or emerging or re-emerging animal diseases shall be recorded and registered promptly and made available to the Chief Veterinary Officer.

ፑ/ የመንግሥትና በግል የተመዘገበ ሐኪም እና ሌሎች የእንስሳት ጤና ባለሙያዎች የበሽታ ቅኝት እና አሰሳ በሚያካሂዱበት ወቅት ማንኛውም ግለሰብ፣ ድርጅት እና ተቋም መረጃ መስጠት እና አስፈላጊውን ትብብር ማድረግ አለበት።

4/ While the government and private veterinarians and veterinary para-professionals conduct surveillance and survey, any individual, organization, and institution shall give the necessary support and collaborate in providing the required information,

፰. ሪፖርት መደረግ ያለበትና አዲስ ወይም እንደገና የተከሰተ በሽታ ስርጭት መከላከል እና መቆጣጠር

8. Prevention and Control of the Spread of Notifiable and Emerging or Re-Emerging Animal Diseases

፩/ ስልጣን ባለው አካል ካልተፈቀደ በስተቀር ማንኛውም ሰው የእንስሳት በሽታ ከገባበት እና ክልከላ ከተደረገበት አካባቢ እንስሳትን፣ የእንስሳት ውጤትን ተረፈ ምርት፣ ባዮሎጂካል ውጤትን፣ በበሽታ አስተላላፊ ተህዋስ የተያዘ ወይም የተበከለ ቁስን ወደ ሌላ ሥፍራ ማንቀሳቀስ አይችልም።

1/ No person shall move an animal, animal products, by-product, biological material, or infected or contaminated article from an infected area except with the permission of the competent authority.

፪/ በማንኛውም በታወቀም ሆነ ባልታወቀ ምክንያት የታመመ ወይም የሞተ እንስሳ ወይም በበሽታ የተበከለ የእንስሳት ዉጤትና ተረፈ ምርት፣ ቁስ እና ማንኛውም ንክኪ ያለው የመገልገያ መሣሪያ ላይ የሳኒተሪ እርምጃ ይወሰዳል።

2/ Sanitary measures shall be taken on any animal that is sick or dead due to a known or unknown cause, or any contaminated animal products, by-products, article and equipment.

፫/ በንዑስ አንቀጽ (፪) የተገለፁትን የታመመ ወይም የሞተ እንስሳ ወይም በበሽታ የተበከለ የእንስሳት ውጤትና ተረፈ ምርት፣ ቁስ እና ማንኛውም ንክኪ ያለው የመገልገያ መሣሪያ ለግል ፍጆታ ማዋልም ሆነ ለገበያ ማቅረብ የተከለከለ ነው።

3/ It is prohibited to use animal that is sick or dead due to known or unknown cause, or contaminated animal product, by-product and articles listed in Sub-Article (2) of this Article for personal consumption or market supply.

፬/ ሪፖርት መደረግ ባለበት ወይም በአዲስ ወይም እንደገና በተከሰተ በሽታ የተያዘ ወይም መያዙ የተጠረጠረ እንስሳ ባለቤት

4/ Any owner of an animal that is infected or suspected to be infected with a notifiable or emerging or re-emerging animal

Scanned with MOBILE SCANNER

ከእንስሳት ጤና አፊሰሩ ወይም ከእንስሳት ጤና ተቆጣጣሪው ፈቃድ ካላገኘ በስተቀር ታማሚውን እንስሳ ከሌሎች ለይቶና አግልሎ ማቆየት አለበት።

5/ ማንኛውም ሰው የእንስሳት በሽታን ለመቆጣጠርና ለመከላከል ሲባል በሚመለከተው አካል ለሚወሰደው የሳኒተሪ እርምጃ ተባባሪ መሆን አለበት።

5/ Any person shall collaborate with any sanitary measures that shall be taken by the competent authority for the purpose of prevention and control of animal disease.

6/ ጉዳዩ የሚመለከተው የእንስሳት ጤና ተቆጣጣሪ ወይም ባለሙያ የታመመው እንስሳ ወይም በበሽታ የተጠቃ አካባቢ ወይም ግቢ ላይ አስፈላጊውን የሳኒተሪ እርምጃ ይወስዳል ወይም እንዲወሰድ ያደርጋል።

6/ The competent veterinary inspector or animal health professional shall take or demand the necessary sanitary measures on infected animals and infected areas or premises.

7/ የሚመለከተው አካል በሃገሪቱ ውስጥ በተወሰኑ አካባቢዎች ኮምፓርትመንት በማቋቋም የእንስሳት በሽታ ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የሚያስችል እርምጃ ሊወስድ ይችላል።

7/ The Competent Authority may establish compartment within specified areas of the country and may take necessary measures for the prevention and control of animal diseases.

፱. ካሣ

9. Compensation

፩/ ስልጣን ያለው አካል የሰውንና የእንስሳትን ሕይወት ወይም ጤንነት ለመከላከልና ቁጥጥር የሚደረግበት የእንስሳት በሽታ እንዳይሰራጭ፣ ተላማች የእንስሳት በሽታ ከመላ ሃገሪቱ ወይም ከተወሰነ የሃገሪቱ ክፍል ለመከላከልና ለመቆጣጠር ሲባል ከማንኛውም ሰው ላይ እንስሳትን ወይም ምርቶችን ከያዘ፣ በሰብዓዊነት የገደለ እና በአግባቡ ያስወገደ እንደሆነ ለባለቤቱ ካሳ ይከፍላል

1/ The Competent Authority shall pay compensation to the owner of animal if the animal or commodity has been the subject of seizure, humane killing, destruction, and disposal in order to protect human and animal life or health and to prevent the entry or spread of a controlled animal disease into or within the territory of the country;

፪/ በንዑስ አንቀጽ (፩) የተጠቀሰው ቢኖርም የእንስሳው ወይም የምርት ባለቤት የምርት ጥራት እና ደህንነት መስፈርት ካላሟላ ወይም እንስሳው የታመመ ሆኖ ወይም የጤና ስጋት ኖሮበት የተወረሰ፣ ሰብዓዊነት ባለው ሁኔታ የተገደለና የተወገደ ከሆነ ካሣ አይከፈልም::

2/ Notwithstanding with Sub-Article (1), no compensation shall be paid if the animal or commodity owner fails to meet the quality and safety standards, or if the animal was diseased, posed a health risk, and was consequently confiscated, humanely killed, and disposed of.

፫/ በንዑስ አንቀጽ (፩) በተጠቀሰው መሠረት በእንስሳት ጤና ባለሙያው ትዕዛዝ መሠረት የእንስሳው በድን እንዲቀበር ወይም እንዲቃጠል ከተደረገ የበድኑ ማስወገጃ ወጪ ለባለቤቱ ይከፈላል፣

3/ In accordance with Sub-Article (1) of this Article when the dead animal is buried or burned upon the instruction of the animal health professional, the expense of disposal shall be paid to the owner

፬/ በተላማች የእንስሳት በሽታ ተይዞ ወደ ኳራንቲን ጣቢያ ውስጥ ለገባና በሰብዓዊ ሁኔታ ለሚወገድ እንስሳ ካሳ አይከፈልም፣

4/ No compensation shall be paid if diseased animals enter in to a quarantine stations and humanely killed..

Scanned with MOBILE SCANNER

፫/ ስለ ካሳ አከፋፈሉ ዝርዝር ይህን አዋጅ ለማስፈፀም በሚኒስቴሩ በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል።

5/ The details of compensation shall be determined by a Directive to be issued pursuant to this Proclamation.

ክፍል አራት

PART FOUR

የእንስሳት ፣ እንስሳት ውጤት እና ተፈሪ-ምርት ልየታ፣ ምዝገባ፣ የጉዞ ቁጥጥር እና ክትትል

ANIMAL, ANIMAL PRODUCT, AND ANIMAL BY-PRODUCT IDENTIFICATION, REGISTRATION, MOVEMENT CONTROL AND TRACEABILITY

፲. የእንስሳት ፣ እንስሳት ውጤት እና ተፈሪ-ምርት ልየታ እና ክትትል ሥርዓት

የእንስሳት ልደትን፣ ሞትን፣ እርድን፣ እንቅስቃሴን፣ በእንስሳት መጠበቂያ ቦታ የሚደረግ ክትትልን፣ የወጪ እና ገቢ እንስሳት አመዘጋገብን እንዲሁም የእንስሳት ውጤቶች እና ተፈሪ-ምርት ልየታና ክትትልን በተመለከተ ሚኒስቴሩ በሃገሪቱ ውስጥ ወጥ የሆነ የልየታ እና ክትትል ሥርዓት ይዘረጋል።

10. Animal, Animal Product and Animal By-Product Identification and Traceability System

The Ministry shall establish identification and traceability system for registration of animal birth, death, slaughter, movement, observation in establishments, and recording of import and export and also an animal product and animal by-product.

፲፩. የእንስሳት ልየታና ምዝገባ

፩/ ማንኛውም በሚኒስቴሩ የብሔራዊ መረጃ ቋት የእንስሳት ዝርያ ውስጥ የተመዘገበ እንስሳ በተናጠል ወይም በመንጋ መለየትና መመዝገብ አለበት።

1/ Any animal of the species registered in the national animal identification and traceability database of the Ministry shall be identified and registered either as an individual or as a herd.

፪/ ስልጣን ባለው አካል ያልተመዘገበና ለመመዝገቡ ማረጋገጫ ያልተሰጠው ሰው መለያዎችን መሸጥ ወይም ለሽያጭ ማቅረብ አይችልም፣

2/ No person shall sell or supply for sale any animal identifier unless he is registered and approved by the Competent Authority.

፫/ መመዝገብ ያለበት እንስሳ ባለቤት ወይም ጠባቂ እንስሳውን የማስመዝገብ እና የተፈቀደውን መለያ ምልክት ለመሸጥ ወይም ለማከፋፈል ፈቃድ ከተሰጠው ሻጭ የመግዛት ግዴታ አለበት፣

3/ The owner or keeper of a registerable animal is obligated to register the animal and to purchase the authorized identification mark from a seller licensed to sell or distribute it.

፬/ የእንስሳው ባለቤት ወይም ጠባቂ ወይም የቄራዎች፣ የእንስሳት ገበያ ወይም የኳራንቲን ጣቢያ ኃላፊ የሆነ ሰው በብሔራዊ መረጃ ቋት ያልተመዘገበ እንስሳ ካለ በአካባቢው ለሚገኝ የእንስሳት ጤና ተቋም ወይም ኃላፊ የማሳወቅ ግዴታ አለበት።

4/ The owner, keeper or a person responsible for a slaughterhouse, animal market, and quarantine stations shall be obliged to notify unidentified and unregistered animals on National Database for the animal health institution or officer responsible for the area.

Scanned with MOBILE SCANNER

፫/ በሚኒስቴሩ ልየታና ምዝገባ ከተደረገላቸው እንስሳት ውጭ ሌሎች እንስሳት ተቀላቅለው የተገኙ እንደ ሆነ የተቀላቀለበት የእንስሳት ባለቤት ለሚመለከተው አካል ሁኔታውን ማሳወቅ አለበት፡፡

፲፪. የእንስሳት ዝውውርን ስለመቆጣጠርና ስለማሳወቅ

፩/ መመዝገብ ያለበትን እንስሳ ማዘዋወር የሚፈልግ ሰው የጉዞ ፈቃድ ለማግኘት ተገቢውን የማመልከቻ ቅጽ በመሙላት ለሚመለከተው አካል ማመልከትና የዝውውር ፈቃድ ማግኘት አለበት፡፡

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) የተጠቀሰው ቢኖርም አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች ለውሃና ግጦሽ ፍለጋ የሚያደርጉትን ዝውውር እና ድንበር ላይ ለሚካሄድ አነስተኛ የእንስሳት ንግድን ተከትሎ የሚደረግ ዝውውርን እንዲሁም የምዝገባ ሥርዓት ባልተዘረጋባቸው ቦታዎች የሚደረጉ ዝውውሮችን አያካትትም፡፡ ነገር ግን በድንበር ዘለል በሽታ ምክንያት የበሽታ ፍንዳታ በሚከሰትበት ወቅት በንዑስ አንቀፅ (1) የተቀመጠው ድንጋጌ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

፫/ እንስሳውን በመጨረሻ ከሚረከበው ተቋም ሲደርስ ለተረካቢው ሰው የእንስሳውን የጉዞ ፈቃድና ተዛማጅ መረጃዎችን አብሮ ማስረከብ አለበት፡፡

፬/ የተመዘገቡ እንስሳት የተላለፈለት ሰው ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ማድረግ አለበት፡፡

፭/ የተመዘገበ እንስሳን የተቀበለ የእንስሳት እርድ ተቋም የእንስሳውን ሙሉ መረጃ ለሚመለከተው አካል ማሳወቅ አለበት፡፡

፮/ አንድ የተለየና የተመዘገበ እንስሳ ቢሞት ወይም ቢሸጥ ወይም ቢጠፋ ወይም ቢሰረቅ ወይም በማንኛውም መንገድ ለሌሎች ቢተላለፍ እንስሳውን በኃላፊነት የያዘው ሰው ለሚመለከተው አካል ማሳወቅ አለበት::

5/ If animals are found to be intermingled with those identified and registered by the Ministry, the owner of the animal should report the matter to the Competent Authority.

12. Animal Movement Control and Notification

1/ A person who intends to move a registrable animal must lodge an application for a veterinary movement permit to a competent authority using the approved form and shall get the permit.

2/ Not withstanding the provision of Sub-Article (1) of this Article, the movement of pastoralists and semi-pastoralists in search of water and pasture, the movement that follows small-scale animal trade conducted at borders, and movements in areas where a registration system has not been established shall not be included. However, in the event of a transboundary animal disease outbreak, the provision set forth in Sub-Article (1) shall be applied.

3/ Upon arrival at the establishment of the destination, the transporter shall furnish the person receiving the animals with the movement permit and any attached documents.

4/ A person who acquires a registerable animal shall notify the competent authority.

5/ Any abattoir which received registered animals shall notify the information to the Competent Authority.

6/ If a registered animal dies, sold, stolen, lost, or transferred to others in any manner, the person responsible for the animal shall notify these conditions to the Competent Authority.

Scanned with MOBILE SCANNER

፲፫. እንስሳትን ለመሰብሰብ ፈቃድ ስለማግኘት

ማንኛውም ሰው እንስሳትን ከተለያየ ቦታ ሰብስቦ በእንስሳት ገበያ ማዕከልም ሆነ በሌላ ሥፍራ ለመያዝ ከፈለገ የእንስሳውን ዓይነት፣ የመጣበትን አካባቢ፣ አጠባበቁን እና አያያዙን የመመዝገብ ሥልጣን ለተሰጠው የሚመለከተው አካል በቅድሚያ አመልክቶ ፈቃድ ማግኘት አለበት፣

ክፍል አምስት
የእንስሳት ጤና ላቦራቶሪ

፲፬. የእንስሳት ጤና ላቦራቶሪ ስለማቋቋም

ማንኛውም የእንስሳት ጤና ላቦራቶሪ ለማቋቋም የሚፈልግ ሰው የወጡ መስፈርቶችን አሟልቶ ሲገኝ ከሚኒስቴሩ ወይም ከክልሉ የእንስሳት ጤና ተቋም የብቃት ማረጋገጫ ማግኘት ይችላል፣፣

፲፭. የእንስሳት ጤና ላቦራቶሪ ስለመሰየም

ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት፡-

፩/ ሚኒስቴሩ እውቅና ያለው የእንስሳት ጤና ወይም የእንስሳት ውጤትንና ተረፈምርትን ደህንነት እና ጥራት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለመስጠት የሚያስችሉ የላቦራቶሪ ምርመራዎችን ፣ ትንተናዎችን ፣ እና ምርምሮችን እንዲያከናውኑ በፌደራል ወይም በክልል ደረጃ የሚቋቋም ወይም ነባር ላቦራቶሪን እውቅና ያለው የእንስሳት ጤና ላቦራቶሪ ብሎ ሊሰይም ይችላል፡

፪/ ሚኒስቴሩ እውቅና ያለውን የፌደራልና የክልል የእንሰሳት ጤና ላቦራቶሪ የሚወጡ መለኪያዎችን አሟልቶ ከተገኘ ብሔራዊ ሪፈራል ላቦራቶሪ ብሎ ሊሰይምና የተወሰኑና ከፍተኛ ደረጃ የላቦራቶሪ ምርመራዎችንና ትንተናዎችን እንዲያከናውን ሊያደርግ ይችላል፡

፫/ ማንኛውም በሚኒስቴሩ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቅት ተሰጥቶት የተመሠረተ የግል የእንስሳት ጤና ላቦራቶሪ የሚወጡ መስፈርቶችን አሟልቶ ከተገኘ እውቅና ያለው የእንስሳት ጤና ወይም የእንስሳት ውጤትንና ተረፈ-ምርትን ደህንነት እና ጥራት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለመስጠት የሚያስችሉ ምርመራዎችንና

13. Approval for Animal Gathering

A person, who intends to gather animals from different areas and hold in market or other shall apply for approval from the Competent Authority responsible to record the species, origins, and conditions of the animals.

PART FIVE
VETERINARY LABORATORIES

14. Establishment of Veterinary Laboratories

Any person who intends to establish a veterinary laboratory shall acquire the certificate of competency from the Ministry or Regional Veterinary Body on fulfillment of requirements.

15. Designation of Veterinary Laboratories

According to directive to be issued by the Ministry:

1/ The Ministry may designate an existing or newly established laboratory at the federal or regional level as an accredited veterinary laboratory to conduct laboratory tests, analyses, and research that will enable it to issue certificates of safety and quality of animal products and by-products;

2/ The Ministry may designate an accredited federal and regional veterinary laboratories as a national referral laboratory if it meets the standards set forth by the Ministry and may authorize it to perform certain high-level laboratory tests and analyses;

3/ Any private veterinary diagnostic or research laboratory established under a certificate of authorization of the Ministry may be designated as an approved veterinary diagnostic or research laboratory for issuance of certificate to perform specific animal health tests, safety and quality of animal products and animal by-product;

Scanned with MOBILE SCANNER

ትንተናዎችን ማድረግ እንዲችል የተፈቀደለት የእንስሳት ጤና ላቦራቶሪ ተብሎ ሊሰየም ይችላል፡

፬/ በንዑስ አንቀጽ (፩) ፡ (፪) እና (፫) የተገለፁት ላቦራቶሪዎች አደረጃጀት፡ አሰያየምና የብቃት ማረጋገጫ መስፈርት በሚኒስቴር መ/ቤቱ በሚወጣ ዝርዝር በመመሪያ ይወሰናል፡፡

4/ The structure, designation and competency requirement of laboratories specified in Sub-Article (1), (2) and (3) shall be determined by Directive to be issued by the Ministry.

ክፍል ስድስት

ወጪ፣ ገቢና ተሻጋሪ ምርት እና ቁጥጥር የሚደረግበት ቁስ ስለመቆጣጠር

PART SIX

THE CONTROL OF EXPORT, IMPORT, AND TRANSIT OF COMMODITIES, AND CONTROLLED ARTICLE

፲፮. ምርትን ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባትንና ማሸጋገርን በተመለከተ ስለሚደረግ ክልከላ

16. Prohibition On Import And Transit Of Commodities

፩/ ማንኛውም ሰው አስፈላጊውን የማስገቢያ ፈቃድ ከባለስልጣኑ እስካላገኘ ድረስ ምርት እና ቁጥጥር የሚደረግበት ቁስን ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት ወይም በሃገሪቷ ድንበር ክልል ውስጥ ማሸጋገር አይችልም፡፡

1/ No person shall import into or convey in transit any commodities, and controlled article through the territory of the country unless he has a permit from the Authority.

፪/ ማንኛውም ሰው የማስገቢያ ፈቃድ ማግኘት የሚችለው ምርት እና ቁጥጥር የሚደረግበት ቁስ ከላኪው ሃገር ከመላኩ በፊት ባለስልጣኑ ያወጣውን መስፈርት ማሟላቱን የሚያረጋግጥ እና በላኪው ሃገር ዕውቅና ባለው ባለሥልጣን የተሰጠ ዓለም አቀፍ የእንስሳት ጤና ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ማቅረብ ሲችል ብቻ ነው፡፡

2/ Any person shall only import commodity and controlled article if it is accompanied by a valid international veterinary certificate issued by the Competent Authority of the exporting country before shipement, which confirms that the sanitary requirements by the Authority have been complied.

፫/ ምርት እና ቁጥጥር የሚደረግበት ቁስ ከውጭ ሃገር መግባት ወይም ወደሌላ ሃገር መሸጋገር የሚችለው በሃገሪቷ በተሰየመ መግቢያ በር ብቻ ወደ ሃገር ውስጥ ሲገባ እና የመግቢያ ፈቃድ በማቅረብ የባለስልጣኑን የእንስሳት ጤና ተቆጣጣሪ ፈቃድ ሲያገኝ ብቻ ነው፡፡

3/ commodities and controlled articles, shall only be imported or transported to another country through a designated entry point in the country and only after obtaining the permission of the competent veterinary inspector by submitting an entry permit.

፬/ ባለስልጣኑ በድንበር አካባቢ ነዋሪ በሆኑ ሰዎች መካከል የሚደረግን ድንበር ተሻጋሪ ልማዳዊና አነስተኛ የእንስሳት ንግድን በተመለከተ አግባብነት ባላቸው ሌሎች ሕጎች መሠረት ያለፈቃድ የሚሰሩበት ሁኔታ የእንስሳት ጤና ቁጥጥርን ግንባቤ ውስጥ ባስገባ መልኩ እንዲተገበር ከሌሎች አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በትብብር ይሰራል፡፡

4/ The Authority shall work in collaboration with other relevant bodies, to ensure that traditional and small-scale cross-border animal trade conducted by residents in border areas, which operates without permits under other relevant laws, is implemented in a manner that takes animal health control into consideration.

Scanned with MOBILE SCANNER

፲፯. የሳኒታሪ እርምጃዎች

፩/ የእንስሳት በሽታ ወይም በሽታ ተሸካሚ ወይም በሽታ አምጪ ተህዋስ ወደሀገር ውስጥ እንዳይገባ ወይም እንዳይሠራጭ ለመከላከል ባለስልጣኑ፦

ሀ) ወደ አገር ውስጥ ከሚገባ ምርት እና ቁጥጥር የሚደረግበት ቁስ ጋር በተያያዘ የሳኒተሪ እርምጃዎችን ይወስናል፣ ተግባራዊም ያደርጋል፣

ለ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ (ሀ) መሠረት የተቀመጡትን የሳኒተሪ መስፈርቶች የማያሟላ ምርት እና ቁጥጥር የሚደረግበት ቁስ ወደ አገር ውስጥ እንዳይገባ ይከለክላል፣ ከገባም እንዲያዝ፣ ወይም እንዲታከም፣ ወይም እንዲወገድ ፣ ወይም ከአገር እንዲወጣ ያደርጋል፣

ሐ) ምርት እና ቁጥጥር የሚደረግበት ቁስ ወደ አገር ውስጥ ሲገባ የጥንቃቄ እና የአስቸኳይ ጊዜ እርምጃ ይወስዳል፣

መ) ምርት እና ቁጥጥር የሚደረግበትን ቁስ በማቆየት የሳኒተሪ እርምጃ ለመውሰድ፣ ለመቆጣጠር፣ ለመመርመር፣ ለማቀነባበር ወይም ለማስወገድ እንዲቻል በኳራንቲን ጣቢያ ቦታነት የሚያገለግሉ የተወሰኑ ቦታዎችን ይሰይማል፣

ሠ) የሳኒተሪ እርምጃዎቹ አወሳሰድ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው ዝርዝር በመመሪያ ይወሰናል።

፪/ በማናቸውም ሁኔታ ወደ አገር ውስጥ በማስገባት ሂደት በሚወሰድ የሳኒተሪ እርምጃ ምክንያት የሚወጡ ወጭዎች የሚሸፈኑት በአስመጭው አካል ይሆናል።

፫/ በዚህ አዋጅ የተቀመጡ የሳኒተሪ እርምጃዎች የሥጋት አሰሳ ላይ የተመሠረቱ እና ዓለም ዓቀፍ የእንስሳት ጤና ድርጅት ካወጣው የየብስ እና የውሃ እንስሳት ሕግ ደረጃዎች ጋር የተጣጣሙ መሆን አለባቸው።

17. Sanitary Measures

1/ To prevent the entry, establishment, or spread of diseases, disease-carrying organisms, or disease-causing organisms, the Authority shall:

a) prescribe and implement sanitary measures related to the importation of commodities and controlled articles;

b) prohibit the entry, if entered detain, or treat or destruct or remove from the country the commodities and controlled articles which do not comply with the sanitary measures prescribed or adopted under Sub-Article (1) paragraph (a) of this Article;

c) take and implement emergency and precautionary measures related to importations of commodities and controlled articles;

d) designate certain places as a quarantine stations where commodities and controlled articles may be kept for sanitary measures, inspection, testing, or further processing or destruction;

e) The details of sanitary measures shall be prescribed by the Directive issued by the Ministry.

2/ In any case, the costs incurred due to sanitary measures taken during the import process will be borne by the importing party.

3/ Sanitary measures mentioned in this Proclamation shall be based on risk assessment and be in accordance with the World Animal Health Organization Terrestrial and Aquatic Animal Health Code.

Scanned with MOBILE SCANNER

፬/ ባለስልጣኑ በዚህ ክፍል የተቀመጡ የሳኒተሪ እርምጃዎች አላስፈላጊ ሲሆኑ ወይም ሁኔታዎች ሲቀየሩ ወይም አዲስ ግኝቶች መኖራቸው ሲረጋገጥ ያለምንም መዘግየት መሻሻላቸውን ወይም መሻራቸውን ያረጋግጣል።

4/ The Authority shall ensure that sanitary measures under this section are modified or revoked without delay if they are no longer necessary, or as conditions change and new findings become available.

፭/ ባለስልጣኑ ሊሟሉ የሚገባቸው የሳኒተሪ እርምጃዎች የተቀመጡበትን ወይም ገደቦችና ክልከላዎች የተደረጉበትን ምክንያት የመግለፅ ግዴታ አለበት።

5/ The Authority shall obliged to make available, the rationale for sanitary requirements restrictions, and prohibitions.

፲፰. ወደ ውጪ ሃገር መላክን በተመለከተ ስለሚደረግ ክልከላና እና ገደብ

18. Restriction and Prohibition on Export

፩/ ማንም ሰው ዓለም አቀፍ የእንስሳት ጤና ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ካልተሰጠው በስተቀር ምርት እና ቁጥር የሚደረግበት ቁስን ወደ ውጪ መላክ አይችልም።

1/ No person may export commodities, and controlled article unless they have been issued with an international veterinary certificate.

፪/ ባለስልጣኑ ወደ ውጭ የሚላከው ምርት ወይም ቁጥር የሚደረግበት ቁስ የበሽታ መንስዔ ወይም ሪፖርት መደረግ ላለበት በሽታ ስርጭት ምክንያት ሊሆን ይችላል ብሎ ሲሰጋ፡-

2/ Where the commodities or controlled article for export poses a risk of infection or spread of a notifiable animal disease, the Authority shall:

ሀ) ዓለም አቀፍ የእንስሳት ጤና ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንዳይሰጥ፤

a) deny issuance of international veterinary certificate;

ለ) ምርቱ እና ቁጥር የሚደረግበት ቁስ በክትትል ሥር እንዲቆይ፤ ወይም

b) keep the commodity or controlled article under observation; or

ሐ) እንደ አስፈላጊነቱም ምርቱ እና ቁጥር የሚደረግበት ቁስ እንዲወገድ ይደረጋል።

c) dispose of the, commodity, or controlled article as deemed appropriate.

መ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ (ሐ) መሠረት የሚወገድ እንስሳ ሰብዓዊነት በተመላበት ሁኔታ መሆን አለበት።

d) An animal disposed of in accordance with Sub-Article 2(c) of this Article must be in a humane manner.

፲፱. የኳራንቲን ተቆጣጣሪ ባለሙያ ሥልጣንና ተግባር

19. Powers and Duties of Quarantine Inspector

፩/ የኳራንቲን ተቆጣጣሪ ባለሙያ ወደ ሃገር ውስጥ የሚገቡ እና ከሃገር የሚወጣ ምርት እና ቁጥር የሚደረግበት ቁስ ላይ በዚህ አዋጅና አዋጁን ለማስፈፀም በሚወጡ ደንብና መመሪያ መሠረት የሳኒተሪ እርምጃ የመውሰድ ሥልጣን አለው።

1/ The Quarantine Inspector has the authority to take sanitary measures on imported and exported commodities and controlled articles in accordance with this Proclamation and Regulation and Directive issued to implement this Proclamation.

Scanned with MOBILE SCANNER

፪/ በንዑስ አንቀጽ (፩) ላይ የተጠቀሰው ቢኖርም የሳኒተሪ እርምጃ ለመውሰድ ጊዜ የሚሰጥ ወይም የሚወሰደው የሳኒተሪ እርምጃ የሚያስከትለው ኢኮኖሚያዊ ጉዳት ከፍተኛ ከሆነ ውሳኔው በበላይ አካል የሚሰጥ ይሆናል።

፫/ በንዑስ አንቀጽ (፩) ከተጠቀሰው ውጪ የኳራንቲን ተቆጣጣሪ ባለሙያው የተሰጠውን ሥልጣን ያለአግባብ ተጠቅሞ ከተገኘ በወንጀል ሕጉ ተጠያቂ ይሆናል።

ክፍል ሰባት

የእንስሳት ውጤት እና ተረፈ-ምርት ደህንነትና ጥራት

፳. ስለ እንስሳት እርድ

፩/ የብቃት ማረጋገጫ ከተሰጠው ቄራ ወይም የሥጋ ማቀነባበሪያ ድርጅት በስተቀር ማንም ሰው እንስሳን አርዶ ሥጋን እና የሥጋ ተረፈ ምርትን ለሽያጭ ማቅረብ አይችልም።

፪/ ኃላፊነት በተሰጠው የሥጋ መርማሪ ተመርምሮ ካልተፈቀደ በስተቀር ለሰው ወይም ለእንስሳት ምግብነት የሚውል ሥጋን ማቅረብ ወይም መሸጥ አይቻልም።

፫/ በቄራ ወይም በሥጋ ማቀነባበሪያ ድርጅት ውስጥ የሚካሄድ የእንስሳት እርድ የሃገር ውስጥ እና የዓለም ዓቀፍ ኮዴክስ አሊሜንታሪየስ ለዚህ ምርት ያስቀመጠውን ደረጃ ያሟላ መሆን አለበት።

፬/ ወደ ውጭ ሃገር የሚላክ ሥጋና የሥጋ ተረፈ-ምርት በተመዘገበ የኤክስፖርት ቄራ የተመረተ፣ በባለስልጣኑ በተሰየመ የሥጋ መርማሪ ደህንነቱ የተረጋገጠና ዓለም አቀፍ የእንስሳት ጤና ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያለው መሆን አለበት።

፭/ የሥጋ እና የሥጋ ተረፈ ምርት ጤንነቱ ከተረጋገጠ የእርድ እንስሳት የተገኘ እና ከበሽታ አምጪ ተህዋስ፣ እድገትን ከሚያፋጥን ንጥረ ነገር እና ከመድሃኒት ቅሪት ነፃ መሆኑን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት ያለው መሆን አለበት።

2/ Notwithstanding the provision of Sub-Article (1) of this Article, sanitary measures shall be taken by higher officials in circumstances where the measure to be taken is not urgent or has a higher economic impact.

3/ The Quarantine Inspector shall be liable according to the Criminal Code if he abuses his power contrary to Sub-Article (1) of this Article.

PART SEVEN

THE SAFETY AND QUALITY OF ANIMAL PRODUCTS AND ANIMAL BY-PRODUCTS

20. Slaughtering of Animal

1/ No person shall slaughter animals and sell the meat and meat by-product other than an authorized abattoir or processing facility which has a certificate of competence.

2/ It is prohibited to sell or supply meat unless it has been inspected and certified as fit for human or animal consumption by the competent meat inspector.

3/ The slaughter conducted in the abattoir or slaughter facility or processing facility shall be in accordance with national and world codex alimentarius safety and quality standards set for this commodity.

4/ Meat and meat by-products destined for export shall come from certified export abattoirs, be confirmed as healthy and fit for human consumption by the meat inspector appointed by the Authority, and shall be accompanied by international veterinary certificate.

5/ Meat and meat by-products shall be accompanied by a veterinary certificate that confirms the product is produced from a healthy animal and confirmed as free from any disease-causing agent, growth hormones, and anti-microbial residues.

Scanned with MOBILE SCANNER

፳፩. ለቄራ፣ የእንስሳት ውጤት ለሚያቀነባብር ድርጅት ስለሚሰጥ የምስክር ወረቀትና ስለሚደረግ ቁጥጥር

፩/ ማንኛውም ሰው፡-

ሀ) በባለስልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ካልተሰጠው በስተቀር ቄራን፣ ለወጪ ንግድ የሚውል የእንስሳት ውጤት እና ተረፈ ምርት ማቀነባበሪያ ድርጅት ማቋቋምና አገልግሎት መስጠት አይችልም፤

ለ) በባለስልጣኑ ወይም በክልል የእንስሳት ጤና ተቋም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ካልተሰጠ በስተቀር ለሃገር ውስጥ ገበያ ሥጋ አቅራቢ የሆነ ቄራን፣ የእንስሳት ውጤት እና ተረፈ ምርት ማቀነባበሪያ ድርጅት ማቋቋምና አገልግሎት መስጠት አይችልም።

፪/ ቄራው ወይም የማቀነባበሪያ ድርጅቱ ተፈላጊውን የግንባታ ደረጃ፣ የአሠራር ሂደት፣ እና የአገልግሎት ክፍያ አሟልቶ መገኘቱን ሲያረጋግጥ እንደ አግባብነቱ የባለስልጣኑ ወይም የክልል የእንስሳት ጤና ተቋም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል።

፫/ የቄራ ወይም የሥጋ ማቀነባበሪያ ድርጅት ግንባታ ደረጃው፣ የጥገና ሁኔታውና የሥራ አመራሩ የተቀመጠውን መስፈርት የሚያሟላ መሆኑን አለመሆኑን ለማረጋገጥ ባለስልጣኑ ወይም የክልሉ የእንስሳት ጤና ተቋም መደበኛ ቁጥጥር ያደርጋል።

21. Certification and Control of Abattoirs, and Animal Product Processing Facilities

1/ No person shall:

a) establish and operate an export abattoir or processing facility for the export of animal product and animal by-product unless he has a certificate of competence from the authority;

b) Establish or operate an abattoir, or animal product and animal by-product processing facility for domestic trade, unless he has a certificate of competence from the Authority or a Regional Veterinary Body.

2/ The Authority or Regional Veterinary Body as appropriate shall issue a certificate of competence only when it confirms that the abattoir, or processing facility complies with standards of construction, operation procedure and service fee.

3/ The Authority or Regional Veterinary Body shall conduct regular inspections to ensure that the abattoir or meat processing facilities are complies with the construction, state of repair, and overall facility management standards.

፳፪. የሥጋ መርማሪ ሥልጣን እና ተግባር

፩/ ከእርድ በፊትና ከእርድ በኋላ በተደረጉ ምርመራዎች ከተገኙ ውጤቶች፣ እንዳስፈላጊነቱም ከሚደረግ የላቦራቶሪ ውጤት በመነሳት በባለስልጣኑ ወይም በክልል የእንስሳት ጤና ተቋም የተሰየመ የሥጋ መርማሪ በሥጋ ምርመራ ደንብ እና መመሪያ መሠረት ያለማንም ጣልቃ ገብነት ውሳኔ የመስጠት ሙሉ ሥልጣን አለው።

፪/ በንዑስ አንቀጽ (፩) ከተጠቀሰው ውጪ ሥጋ መርማሪው የተሰጠውን ሥልጣን ያለአግባብ ተጠቅሞ ከተገኘ በወንጀል ሕጉ መሠረት ተጠያቂ ይሆናል።

22. Powers and Duties of a Meat Inspector

1/ The meat inspector assigned by the authority or the regional veterinary body shall have power to pass decision according to Meet Inspection Regulations and Directives based on the findings of anti-mortem and post-mortem inspection, laboratory test results as deemed necessary without the interference of other bodies.

2/ The meat inspector shall be liable according to the Criminal Code if he abuses his power contrary to Sub-Article (1) of this Article.

Scanned with MOBILE SCANNER

፳፫. <u>የእንስሳት ውጤት ስለማምረት፣ ስለማቅረብና ስለማቀነባበር</u>

፩/ የእንስሳት ውጤት እና ተረፈ ምርት የሚያስገኙ እንስሳት እና መንጎች የጤና ሁኔታ በሕብረተሰብ ጤና ላይ ጉዳት በማያደርስ ሁኔታ መያዝ እና መመራቱን በሕግ ሥልጣን የተሰጠው አካል ይቆጣጠራል።

፪/ የእንስሳት ውጤት እና ተረፈ ምርት ጥራትና ደህንነት የኮዴክስ አሊመንታሪየስ መርሆዎችን ተከትሎ ባለስልጣኑ በሚያስተምጠው መስፈርት መሠረት መረጋገጥ አለበት።

፫/ በባለስልጣኑ ወይም በክልል የእንስሳት ተቋም ቁጥጥር ካልተደረገበት፣ ካልተመረመረ እና ደህንነቱ ካልተረጋገጠ በስተቀር ለሰው ምግብነት የእንስሳት ውጤት ለሽያጭ መቅረብ አይችልም።

፬/ ለሰው ምግብነት በሽያጭ የሚቀርብ የእንስሳት ውጤት ከማንኛውም በሽታ አምጪ ተህዋስ እና ከመድሃኒት ቅሪት ነፃ መሆኑ የተረጋገጠ መሆን አለበት።

<u>ክፍል ስምንት</u>

<u>የእንስሳት ደህንነትን ስለማስጠበቅ እና ስለመቆጣጠር</u>

፳፬. <u>የእንስሳት ባለቤት ወይም እንስሳትን የሚይዝና የሚንከባከብ ሰው ኃላፊነት</u>

ማንኛውም የእንስሳት ባለቤት ወይም እንስሳትን የሚይዝና የሚንከባከብ ሰው ለእንስሳው፡-

፩/ በቂ የእንስሳት መኖ የማቅረብ፣

፪/ በቂ እና ንጹህ ውሃ የማቅረብ፣

፫/ ከእንስሳው ባሕርይ እና ከአየር ጠባዩ ጋር የሚስማማ ምቹ መጠለያ የማቅረብ፣

፬/ የተሟላ የእንስሳት ሕክምና እና ክትባት እንዲያገኙ የማድረግ፣

፭/ አግባብነት ያለው አያያዝ እና ጥበቃ እንዲያገኙ የማድረግ፣

፮/ ተገቢውን ደረጃ በሚያሟላ ማጓጓዣ የማጓጓዝ፣ እና

23. <u>Production, Supply, and Processing of Animal Products</u>

1/ The authoritrized body given by law, shall regulate the health status of animals and herds which produce animal product and animal by-products are maintained and managed in a manner that minimizes or avoids public health risks.

2/ The safety and quality of animal product and by-products shall be ensured according to the standard set by the Authority as per the principles of Codex Alimentarius

3/ Animal product supplied for human consumption shall not be sold unless it is inspected, tested, and certified for its safety by the Authority and Regional Veterinary Body.

4/ Animal product sold for human consumption shall be confirmed to be free from any disease-causing agent and antimicrobial residue.

<u>PART EIGHT</u>

<u>ANIMAL WELFARE PROTECTION AND CONTROL</u>

24. <u>Responsibility of Animal Owner or Person Responsible for the Care and Handling of Animals</u>

Any owner or person responsible for the care and handling of an animal shall be responsible to provide the animal with:

1/ sufficient animal feed;

2/ sufficient and clean water;

3/ proper housing appropriate for their behaviors and weather conditions;

4/ appropriate veterinary health care and vaccination;

5/ proper care, handling and protection;

6/ transportation of animals with conveys that meets animal welfare standards; and

Scanned with MOBILE SCANNER

፯/ በእርጅና እና በበሽታ ወይም በሌላ አስገዳጅ ምክንያት መወገድ ካለበት ለሚመለከተው አካል የማሳወቅ፡

ኃላፊነት አለበት።

7/ information to the concerned body if the animals shall be culled due to old age, illness or other compelling reasons.

፳፭. <u>እንስሳትን በጭካኔ መንገድ መያዝ የተከለከለ ስለመሆኑ</u>

25. <u>Prohibition of Cruel Handling of Animals</u>

፩/ ማንኛውም ሰው የሚከተሉትን ድርጊቶች በእንስሳት ላይ መፈፀም የለበትም፡-

ሀ) እንስሳትን በጭካኔ ማሰቃየት ፡ መደብደብ፡ መጉዳት ወይም አካላቸውን ማቁሰል ወይም መቁረጥ ፡

ለ) እንስሳት ከአቅማቸው በላይ መጫን ወይም ማሠራት፡ ወይም

ሐ) እንስሳትን ሆን ብሎ ወይም በቸልተኝነት አላግባብ መያዝ ወይም ጭካኔ በተሞላው ሁኔታ ጉዳት ማድረስ።

1/ No person shall perform the following acts on animals:

a) torture, beat, injure or mutilate any animal with cruelty;

b) overload or overwork any animal; or

c) Intentionally or negligently maltreat or abuse, any animal in a cruel or inhumane manner.

፪/ በእንስሳት ላይ ህመምን ወይም ስቃይን የሚያስከትል ወይም ምቾትን የሚነሳ የእንስሳት እርባታ ዘዴ ማካሄድ የተከለከለ ነው።

2/ an animal husbandry practice that may cause pain or suffering or discomfort to animals is prohibited.

፫/ ስለ እንስሳት ጥበቃ እና ደህንነት ዝርዝር አሠራሩ በደንብ ይወሰናል።

3/ the details on animal welfare shall be provided in a Regulation

፳፮. <u>እንስሳት ላይ ሙከራና ምርምር ስለማድረግ</u>

26. <u>Conducting Research and Experiment on Animal</u>

ማንኛውም ሰው በእንስሳት ላይ ሙከራና ምርምር ለማካሄድ ከሚኒስቴሩ ወይም ከተገቢው የመንግስት አካል ፈቃድ ማግኘት አለበት።

Any person shall acquire permission from the Ministry or the Appropriate Government Authority to conduct an experiment and research on an animal.

፳፯. <u>እንስሳት ለኤግዚቢሽን ወይም ለመዝናኛ እንዲያዙና ተከልለው እንዲቀመጡ ስለሚፈቀድበት ልዩ ሁኔታ</u>

27. <u>Special Conditions on Capture and Confinement of Animals for Exhibition or Public Entertainment</u>

ማንኛውም ሰው መካነ እንስሳት፡ ሰርከስ፡ ወይም በጊዜያዊነትም ሆነ በቋሚነት እንስሳትን አግልሎ በአንድ ሥፍራ ማስቀመጫ ማቋቋም የሚችለው ከሚኒስቴሩ ወይም ከሚመለከተው የመንግስት አካል የብቃት ማረጋገጫ ሲያገኝ ብቻ ነው።

Any person shall establish a zoo, circus or any other permanent or temporary facility for the confinement of animals, only when he has a certificate of competency from the Ministry or concerned Government Body.

፳፰. <u>መንገድ ላይ ያለባለቤት ጥበቃ መውጣቱ የተጠረጠረ እንስሳን ሪፖርት የማድረግ ግዴታ</u>

28. <u>Obligation to Report a Suspected Unguarded Stray Animal</u>

፩/ ማንኛውም የእንስሳው ባለቤት እንስሳው ያለፈቃዱ መንገድ ላይ መውጣቱን ሲያውቅ በቅርብ ለሚገኝ እንስሳት ጤና ተቋም ወይም

1/ Any animal owner who knows that his animal is on the road without his permission is obligated to report to the

Scanned with MOBILE SCANNER

ባለሞያ ወይም ለአካባቢ አስተዳደር ሪፖርት ማድረግ ይኖርበታል።

፪/ ባለቤት አልባ እንስሳ ማግኘቱን የጠረጠረ የአካባቢ ሰው በቅርብ ለሚገኝ የእንስሳት ጤና ተቋም ወይም ባለሞያ ወይም ለአካባቢው አስተዳደር ሪፖርት ማድረግ ይኖርበታል።

፫/ የእንስሳት ጤና ተቋም እና የአካባቢው አስተዳደር በደረሰው ሪፖርት መሠረት አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል።

2/ Any member of the the community who found a suspected stary animal is obligated to report to the nearest veterinary institution, professional or local administration.

3/ The Veterinary Authority and Local Administration shall take necessary action based on the report.

፳፱. የእንስሳት ደህንነትን በተመለከተ በትብብር ስለመስራት

ሚኒስቴሩ የእንስሳት ደህንነትን በተመለከተ ሌሎች በሕግ ስልጣን ከተሰጣቸው ተቋማት ጋር በትብብር ይሰራል።

29. Work with Collaboration on Animal Welfare

The Ministry shall work in collaboration on animal welfare with other bodies authorized by relevant laws.

ክፍል ዘጠኝ

የሚኒስቴሩ፣ የባለስልጣኑ እና የክልል እንስሳት ጤና ተቋም ሥልጣንና ተግባር

PART NINE

THE POWERS AND DUTIES OF THE MINISTRY, AUTHORITY, AND REGIONAL VETERINARY BODY

፴. የሚኒስቴሩ ሥልጣንና ተግባር

ሚኒስቴሩ፣

፩/ የእንስሳት ሀኪም የሆነ የሃገሪቱን ዋና የእንስሳት ጤና አገልግሎት ኦፊሰር ይመድባል፤

፪/ ብሔራዊ የእንስሳት ጤና የመረጃ ሥርዓትን ይዘረጋል፤

፫/ አስቸኳይ የሳኒታሪ እርምጃ መውሰድ የሚያስችል የድንገተኛ በሽታዎች ዝግጁነት እቅድ ያዘጋጃል፣ በጀት እንዲመድብ ያደርጋል፣ ከክልል የእንስሳት ጤና ተቋም ጋር በመተባበር እቅዱን ተግባራዊ ያደርጋል፤

፬/ ዓለም ዓቀፍ የእንስሳት ጤና ድርጅት ባወጣው መስፈርት እና በአገሪቱ የእንስሳት ጤና ሳኒተሪ ደረጃ መሠረት ሪፖርት መደረግ ያለበት የእንስሳት በሽታ ዝርዝር ያዘጋጃል፣ ያፀድቃል፣ እንደአስፈላጊነቱ ያሻሽላል፤

30. The Powers and Duties of the Ministry

The Ministry shall:

1/ Appoint a Country's Chief Veterinary Officer who is a veterinarian;

2/ Establish a national animal health information system;

3/ Develop an emergency disease preparedness plan that enables the implementation of sanitary measures, allocate a dedicated budget, and operationalize the plan in collaboration with the Regional Veterinary Body;

4/ Develop and update a national list of notifiable animal diseases based on the world animal health organization requirement and the sanitary status of the country;

Scanned with MOBILE SCANNER

ሸ/ አዲስ የተከሰተ፣ እንደገና የተከሰተ፣ እና ሪፖርት መደረግ ያለበት ሆኖ በቁጥጥር ስር የዋለ እና ቁጥጥር የሚደረግበት የእንስሳት በሽታን ዓይነት ለሚመለከታቸው ሃገራዊ፣ አህጉራዊ እና ዓለም አቀፋዊ አካላት ያሣውቃል፣

ቀ/ የእንስሳት በሽታ ቅኝት፣ እና ቁጥጥር ሥርዓትን ይዘረጋል፣

በ/ ከእንስሳት ወደ ሰው የሚተላለፉና የማይተላለፍ በሽታዎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር እንዲሁም ከእንስሳት የሚገኝ ምግብን ደህንነትና ጥራት ለማረጋገጥ የሚያስችል ሥርዓት ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ይዘረጋል በጋራ ያስፈጽማል፣

ተ/ የእንስሳት በሽታን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠርና ለማጥፋት የሚያግዙ አስፈላጊ የሳኒታሪ እርምጃ ይወስዳል፣

ቸ/ የእንስሳት በሽታን ለመከላከል ወይም የእንስሳት በሽታ ፍንዳታ ሊያስከትላቸው የሚችላቸውን ሥጋቶች ለመቀነስ ሲባል ለሚወገዱ እንስሳት የካሳ ክፍያ ሥርዓት ያዘጋጃል፣ ተግባራዊም ያደርጋል፣

ኀ/ አንድ ቦታ የእንስሳት በሽታ ያለበት ወይም በእንስሳት በሽታ የተበከለ፣ ወይም ከበሽታ ነፃ የሆነ፣ በሽታው ያለበትን ቦታ ከሌለበት የሚለይ ድንበር ወይም በሽታው በዝቅተኛ ደረጃ የሚገኝበት መሆኑን ያውጃል፣

ነ/ ሪፖርት መደረግ ባለበት የእንስሳት በሽታ ተጠቅቶ የነበረ አካባቢ ከበሽታው ነፃ መሆኑን አረጋግጦ ያውጃል፣

ኘ/ የእንስሳት እና እንስሳት ውጤቶችና ተረፈ-ምርት ልየታ፣ ምዝገባና የክትትል ሥርዓትን ይዘረጋል፣ ብሔራዊ ምዝገባ መረጃ ቋትን ያደራጃል፣

አ/ የምርምር እና የስልጠና ተቋማት እንዲቋቋሙ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ ያደራጃል፣

ኸ/ የእንስሳት ጤና ባለሞያዎችን ትምህርት፣ ሥልጠና ሥነ-ምግባርና ብቃት ማሳደግን በተመለከተ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ይሰራል፣

ወ/ ብሔራዊ ጠቀሜታ ያላቸውንና ልዩ ዕውቀትና ክህሎት የሚጠይቁ የምርምርና የቁጥጥር ተግባራትን እንዲከናወኑ ያደርጋል፣

5/ declare a type of emerging, re-emerging, notifiable under control, and controlled animal diseases for National, Regional and International Organizations;

6/ Develop a system for animal disease surveillance and control;

7/ Design and implement a system in collaboration with relevant stakeholders that enables the prevention and control of both zoonotic and non-zoonotic diseases, as well as ensure the safety and quality of food derived from animals;

8/ Take the necessary sanitary measure,in order to prevent, control, and eradicate animal disease;

9/ Develop and implement a system of compensation for animals culled to prevent disease or reduce the risks associated with animal disease outbreaks;

10/ Declare areas as infected, free from disease, buffer zone, and areas of low prevalence;

11/ Declare area infected with notifiable disease as free area;

12/ Establish animal, animal product and animal by-product identification and traceability system. organize national registration data base;

13/ Facilitate and organize the establishment of research and training institutions;

14/ Work in collaboration with relevant bodies to ensure the education, training, ethics, and competency development of animal health professionals;

15/ Ensure the accomplishment of nationaly impotant regulatory and research activities that need special knowledge and skill;

Scanned with MOBILE SCANNER

፲፮/ ለእንስሳት ጤና ምርመራ ላቦራቶሪዎች የሥራ ፈቃድ እና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሠጣል፣ አስፈላጊ ሲሆንም የሰጠውን ፈቃድ እና ብቃት ያግዳል ወይም ይሠርዛል፣

16/ Issue work permit and certificate of competency for veterinary diagnostic laboratories and suspend or revoke when it deems necessary;

፲፯/ የእንስሳት ጤና አገልግሎትን ጥራትና ተደራሽነት ለማሻሻል የሚያስችሉ ሥርዓቶችንና መሠረተ ልማቶችን ይዘረጋል፣ እንደአስፈላጊነቱ ላቦራቶሪዎችና ክሊኒኮች እንዲገነቡ ያደርጋል፣ አትማቸውን ይገነባል፣ ውጤታማነታቸውን ያረጋግጣል፣

17/ Establish a system and infrastructure that enable to improve the quality and accessibility of veterinary services; couse to construct laboratories and clinics as deems necessary and build their capacity and monitor their effectiveness;

፲፰/ የእንስሳት ጤና ላቦራቶሪዎችን እና የእንስሳት ጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማትን ደረጃ ይወስናል፣

18/ Determine the level of veterinary laboratories and veterinary service delivery establishments;

፲፱/ የግል የእንስሳት ጤና አገልግሎት እንዲስፋፉ ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል፣

19/ Create conducive environment for private veterinary services development;

፳/ የመንግሥት እና የግል የእንስሳት ጤና አገልግሎቶችን ሚና እና ኃላፊነት ይወስናል፣

20/ Set the role and responsibility of public and private veterinary services;

፳፩/ በሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በእንስሳት ጤና እና ደህንነት ዙሪያ የሚሰሩ መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማትን ይከታተላል ድጋፍም ያደርጋል፣

21/ Without prejudice to provisions of civil society organizations' proclamation, supervise and support non-governmental organizations working on animal health and welfare;

፳፪/ እውቅና የተሰጣቸው የግል የእንስሳት ሀኪሞች፣ ሌሎች የእንስሳት ጤና ባለሙያዎች እና የእንስሳት ጤና አገልግሎት የሚሰጡ ድርጅቶች የሳኒታሪ ማንዴት ውል ወስደው የተወሰኑ ሥራዎችን ለማከናወን ወይም የተወሰኑ ኃላፊነቶችን ለመተግበር የሚያስችሏቸውን መስፈርቶች ያወጣል፣ እንዳስፈላጊነቱ የሳኒታሪ ማንዴት ውል ይሰጣል፣

22/ It establishes the requirements for accredited private veterinarians, veterinary professionals and animal health service institutions to obtain a sanitary mandate contract and perform certain defined functions or exercise powers; it issues sanitary mandate contracts as necessary;

፳፫/ የእንስሳት ደህንነትን ለማስጠበቅ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣

23/ Establish a system to ensure animal welfare;

፳፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬)፣ (፭)፣ (፲) እና (፲፩) የተዘረዘሩትን እወጃዎች ወይም ማሻሻያዎች በመገናኛ ብዙሃን ለሕዝብ ይፋ ማድረግ እና ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በጽሁፍ እንዲደርሱ ያደርጋል፣

24/ Make available declarations or amendments stated under Sub-Article (4), (5) (10), and (11) of this Article to the public and shall notify all relevant stakeholders in writing;

Scanned with MOBILE SCANNER

፳፫/ የእንስሳት ጤናን፣ ደህንነትንና በእንስሳት ህክምና የሕብረተሰብ ጤናን ለመጠበቅ የሚያስችል የግንዛቤ ማሳደጊያ ሥራ ይሠራል፤

፳፮/ ይህን አዋጅ ለማስፈፀም ከሌሎች የሚመለከታቸው አካላት ጋር በትብብር ይሰራል፤

፳፯/ ማናቸውንም በዚህ አዋጅ የተቀመጡ ድንጋጌዎች ተግባራዊ ለማድረግ እና ለማስፈፀም ለክልል የእንስሳት ጤና ተቋም ውክልና ይሰጣል።

፴፩. <u>የባለሥልጣኑ ሥልጣንና ተግባር</u>

፩/ የእንስሳት በሽታ ከውጭ ሀገር እንዳይገባ ወይም በሀገር ውስጥ እንዳይሠራጭ ለማድረግ በድንበር አካባቢ ነዋሪ በሆኑ ሰዎች መካከል ለግል መጠቀሚያ ሲባል የሚደረግ የእንስሳት ግብይት እንደተጠበቀ ሆኖ ገቢ እና ተሸጋጋሪ ምርት እና ቁጥጥር የሚደረግበት ቁስን በመቆጣጠር እንደአስፈላጊነቱ የሳኒታሪ እርምጃ ይወስዳል።

፪/ ወደ ሃገር ውስጥ ለሚገባ ምርት ወይም ቁጥጥር የሚደረግበት ቁስ የማስገቢያ መስፈርት ያወጣል፤ በመስፈርቱም መሠረት የማስገቢያ ፈቃድ ይሠጣል።

፫/ በዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለስልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፭፻፸፭/፪ሺ አንቀጽ ፮ ንዑስ አንቀጽ (፭) ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በዓለም አቀፍ ደረጃ ሪፖርት መደረግ ያለባቸው የእንስሳት በሽታዎችን በተመለከተ ወጪ የሚደረግ ምርት ወይም ቁጥጥር የሚደረግበት ቁስ አስፈላጊውን መስፈርት አሟልቶ ሲገኝ ዓለም አቀፍ የእንስሳት ጤና ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሠጣል።

፬/ ለኤክስፖርት እና ከአንድ ክልል በላይ ለሚደረግ ግብይት የሚያመርት ቄራ እና የእንስሳት ውጤት እና ተረፈ ምርት ለሚያቀነባብር ድርጅት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሠጣል፤ ቁጥጥር ያደርጋል፤ እንደአስፈላጊነቱም ያግዳል ወይም ይሠርዛል።

፭/ የኳራንቲን ቦታዎችን ይለያል ወይም ይወስናል፤

25/ accomplish awareness creation activities to protect animal health, welfare and veterinary public health;

26/ Work in collaboration with other stakeholders to implement this Proclamation;

27/ Delegate Regional Veterinary Body to implement and enforce the provisions of this Proclamation.

31. <u>Powers and Duties of the Authority</u>

1/ Without prejudice to petty trade among the border community, take sanitary measures as may be necessary, in order to prevent the entry into or the spread of animal disease within the country by controlling the import and transit of commodity and controlled article.

2/ Set import requirements and accordingly issue import permit for commodity and controlled articles.

3/ Without prejudice to Article 6 Sub-Article (5) of Wildlife Development and Conservation Proclamation No. 575/2008, issue international veterinary certificates upon fulfillment of necessary requirements for the export of commodity and controlled articles regarding international notifiable animal diseases.

4/ Issue certificates of competency for export abattoirs and abattoirs that market for more than one regional state and animal products and by-product processing facilities; and control their activities, when it deems necessary, suspend or revoke the certificate of competency.

5/ Identify or Designate quarantine areas.

Scanned with MOBILE SCANNER

፮/ ምርት እና ቁጥጥር የሚደረግበት ቁስ ከአገር በሚወጡባቸው እና ወደ አገር በሚገቡባቸው ቦታዎች ላይ የኳራንቲን ማዘዣዎችን ያቋቁማል፤፤

6/ Establish quarantine stations at border points through which commodity and controlled article destined for export and import pass.

፯/ ምርት እና ቁጥጥር የሚደረግበት ቁስ ወደ አገር ውስጥ የሚገባበትን እና ከአገር የሚወጣበትን መቆጣጠሪያ ማዘዣ ይለያል፣ ያቋቁማል፤፤

7/ Designate and establish the ports of entry and exit for import and export of commodity and controlled article.

፰/ ከእንስሳት የሚገኝ ውጤት እና ተረፈ ምርት ጥራት እና ደህንነት ለማረጋገጥ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በትብብር ይሠራል፤፤

8/ Work in collaboration with the relevant bodies for ensuring the quality and safety of animal products and animal by-product

፱/ ለቄራ፣ የእንስሳት ውጤት እና ተረፈ ምርት ለሚያቀነባብር ድርጅት የማንሳት፣ የአሰራርንና ቁጥጥር የሚደረግበትን ሌሎች ዝርዝር መስፈርቶችን፣ ደረጃዎችን ያወጣል፣ የአሰራር ሥርዓትንም ይዘረጋል፣

9/ Develop detailed standards and procedures and establish a system for the construction, operation, and control of abattoir and animal product and animal by-product processing plant

፲/ የምርት ጤና፣ ጥራትና ደህንነትን ለማስጠበቅ የሚያስችሉ ሌሎች የቁጥጥር ተግባራትን ይፈፅማል፤፤

10/ Perform other regulatory duties related to the health, safety, and quality of commodities.

፲፩/ ለክልል የእንስሳት ጤና ተቋማት እንዳስፈላጊነቱ ውክልና ይሰጣል፤፤

11/Delegate its power to Regional Veterinary Body as deemed necessary.

፴፪. ዋና የእንስሳት ጤና ኦፊሰር

32. The Chief Veterinary Officer

፩/ በሃገሪቱ የእንስሳት ጤናን፣ ደህንነትንና በእንስሳት ህክምና የሕብረተሰብ ጤናን ለመጠበቅና ለመቆጣጠር የሚያስችሉ ተግባራትን ያስተባብራል፣ ይመራል እና አስገዳጅ ውሳኔዎችን ይሰጣል፤፤

1/ Shall be responsible for coordinating, leading, and making mandatory decisions that are required to regulate the country's animal health, welfare, and veterinary public health activities.

፪/ ሃገሪቱን በዓለም አቀፍ የእንስሳት ጤና ድርጅት እና በሌሎች ዓለም አቀፍ መድረኮች ይወክላል፣ የዓለም አቀፍ የእንስሳት ጤና ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አሰጣጥ ሥርዓትን በበላይነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል፤፤

2/ shall represent the country on the world animal health organization and other international platforms; lead and control the overall system for issuance of international veterinary certificates.

፫/ የክልል የእንስሳት ጤና ተቋም የእንስሳት ጤና ባለሙያ የሆነ አንድ የክልል ዋና የእንስሳት ጤና ዳይሬክተር ይኖረዋል፣ ከዋናው የእንስሳት ጤና ኦፊሰር ጋር ቀጥተኛ የስራ ግንኙነትም ይኖረዋል፤፤

3/ Regions shall also have a regional Director of veterinary Services assigned by the regional veterinary body and he shall directly communicate with the Chief Veterinary Officer.

Scanned with MOBILE SCANNER

፴፫. የክልል የእንስሳት ጤና ተቋም ተግባርና ኃላፊነት

የክልል የእንስሳት ጤና ተቋም የሚከተሉት ኃላፊነትና ተግባራት ይኖረዋል፡-

ሀ/ ለዋናው የእንስሳት ጤና ኦፊሰር ተጠሪ የሚሆን የክልል የእንስሳት ጤና ዳይሬክተር ይሰይማል፤

ለ/ ሪፖርት መደረግ ያለበትን አዲስ ወይም እንደገና የተከሰተ የእንስሳት በሽታ ለመቃኘት፣ ለማሰስ፣ ለመከላከልና ለመቆጣጠር ከሚኒስቴሩ፣ ከባለስልጣኑና ከአጎራባች ክልሎች ጋር በትብብርና በቅርበት ይሠራል፤

ሐ/ ማንኛውም የክልል የእንስሳት ጤና ባለሞያ ሪፖርት መደረግ ያለበትን አዲስ ወይም እንደገና የተከሰተ የእንስሳት በሽታ መከሰቱን ሲጠረጠር ወይም ሲያረጋግጥ በአንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፫) በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መሠረት ለክልሉ የእንስሳት ጤና ተቋም ሪፖርት ማድረጉን ያረጋግጣል፤

መ/ ሪፖርት መደረግ ያለበት ወይም አዲስ ወይም እንደገና የተከሰተ የእንስሳት በሽታ መከሰቱን የሚያጠራጥር ወይም የሚያረጋግጥ ማንኛውም ሪፖርት ሲደርሰው በማንኛውም ፈጣን የመረጃ መለዋወጫ መንገድ ለሚኒስቴሩ ዋና የእንስሳት ጤና ኦፊሰር ያሳውቃል፤

ሠ/ ሪፖርት መደረግ ያለበት በሽታን ለመቃኘትና ለመዳሰስ፣ ለመከላከልና ለመቆጣጠር የተነደፈ ፕሮግራም ሲተገበር የእንስሳት ባለቤቶችንና በየደረጃው የሚገኙ ባለድርሻ አካላትን ያሳትፋል፣ ያስተባብራል፤

ረ/ ሚኒስቴሩ በሚያወጣቸው ደረጃዎች መሠረት የግል የእንስሳት ጤና ባለሙያ ወይም ተቋም የተወሰኑና በግልፅ የተቀመጡ ተግባራትንና ኃላፊነቶችን እንዲያከናውኑ የሳኒተሪ ማንዴት ውል ይሰጣል፤

ሰ/ የእንስሳት ጤና አገልግሎት እና የእንስሳት ውጤት እና ተረፈ ምርት ላቦራቶሪ በክልሉ ያደራጃል፣ እውቅና እንዲያገኙ ይሰራል፤

33. The Duties and Responsibilities of the Regional Veterinary Body

The Regional Veterinary Body shall have the following duties and responsibilities:

1/ Appoint a Regional Veterinary Director who shall be accountable to the Chief Veterinary Officer of the country;

2/ Collaboratete and work closely with the Ministry, the Authority, and neighboring regions for the surveillance, survey, prevention, and control of notifiable, emerging, and re-emerging animal diseases;

3/ Ensure that any regional animal health professionals provides reports of any suspected or confirmed occurrence of a notifiable or emerging and re-emerging animal disease for regional veterinary body as per the time period prescribed under Sub-Article (2) and (3) of Artcle 6;

4/ Notify any reports of the suspected or confirmed occurrence of a notifiable or emerging and re-emerging animal disease to the chief veterinary officer of the Ministry by the fastest communication means possible;

5/ Coordinate and ensure collaboration with animal owners, and other different levels of stakeholders during the implementation of surveillance, prevention and control program of notifiable, emerging, and re-emerging animal diseases;

6/ give the sanitary mandate contract to private veterinarians and institutions to perform certain defined functions and exercise certain responsibility as per the standards developed by the Ministry;

7/ Organize regional veterinary service and animal product and animal by-product diagnostic laboratories and work to ensure their accreditation;

Scanned with MOBILE SCANNER

፰/ ለኤክስፖርት እና ከአንድ ክልል በላይ ለሚደረግ ግብይት የሚያመርት ቄራ እና የእንስሳት ውጤት እና ተዋጽኦ ከሚያቀነባብር ድርጅት በስተቀር በሌሎች ቄራዎች ላይ የጤና፣ የጥራትና ደህንነት ቁጥጥር ያደርጋል፣ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ እንደ አስፈላጊነቱም ይሰርዛል፣

፱/ የእንስሳት በሽታ መረጃ ለመሰብሰብ፣ ለማጠናቀር እና ለመተንተን የሚያስችል የመረጃ ሥርዓት ለመዘርጋት ከሚኒስቴሩ ጋር በቅንጅት ይሰራል ፣

፲/ የእንስሳት ጤናን፣ ደህንነትን እና በእንስሳት ሕክምና የጎበረተሰብ ጤናን በክልሉ ለማረጋገጥ ከሚኒስቴሩ ወይም ከባለስልጣኑ በውክልና የወሰዳቸው ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።

፴፬. የእንስሳት ጤና እና ደህንነት ተቆጣጣሪ ሥልጣንና ተግባር

፩/ በሚኒስቴሩ ወይም በባለስልጣኑ ወይም በክልል የእንስሳት ጤና ተቋም የተመደበ ተቆጣጣሪ፡-

ሀ) ይህን አዋጅና አዋጁን ለማስፈፀም የሚወጡ ደንብና መመሪያ መከበሩን ማረጋገጥ፣

ለ) ለአካባቢው የእንስሳት ጤና ተቋም በደረሰ መረጃ መሠረት በማንኛውም ቅጥር ግቢ በመግባት የሳኒተሪ እርምጃ የመውሰድ፣

ሐ) ለአካባቢው የእንስሳት ጤና ተቋም በደረሰ መረጃ መሠረት በማንኛውም ቅጥር ግቢ ወይም ድርጅት ውስጥ በሥራ ሰዓት የመግባት፣ ምርመራ የማካሄድ፣ ናሙና የመውሰድ፣ የማሸግ፣ የላቦራቶሪ ምርመራ ውጤት እስኪታወቅ ድረስ ምርቱ ለብቻ ተለይቶ እንዲቀመጥ የማዘዝ እና ምልክት የማድረግ፣ በሕግ አግባብ ምርቱን የማገድ እና የመያዝ ወይም ምርቱ ወይም ከምርቱ ጋር የሚያያዝ ቁስ ካለበት ቦታ ሳይወጣ ወይም በምንም ዓይነት ሁኔታ ሳይቀየር እንዲከማች ወይም ኳራንቲን እንዲደረግ የማዘዝ፣

8/ Inspect and issue certificates of competency for domestic abattoirs and other processing facilities of animal products and revoke when necessary, except for export abattoirs and abattoirs which produce and market for more than one region,

9/ Work jointly with the Ministry to establish a system for the collection, recording, and analysis of animal disease information;

10/ Perform other activities delegated by the Ministry or Authority to ensure animal health, welfare, and veterinary public health in the region.

34. Powers and Duties of Animal Health and Welfare Inspector

1/ An inspector appointed by the Ministry or the Authority or Regional Veterinary Body shall have the following powers and duties:

a) ensure this Proclamation and Regulations and Directives issued under this Proclamation are compiled;

b) Take sanitary measures by entering any premises as per the information given for local veterinary body.

c) enter in to any premises or institution during working hours, conduct the investigation, take sample, order its temporary closure, order a commodity to be kept separately until laboratory result is known; mark, to detain and seize, or order the storage or quarantine any commodity or another thing related to the commodity without removal or alteration as per the information given for local veterinary body.

Scanned with MOBILE SCANNER

መ) ማንኛውንም ምርት እና ቁጥጥር የሚደረግበት ቁስ የሜን ማንቀሣ የማስቆም፣ የመመርመር፣ የመክፈት፣ ናሙና የመውሰድ እና የማገድ እና የመያዝ ፣ ውሳኔውን በሺ፸ ሰዓት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የማሳወቅ፣

d) To stop any vehicle or other means of transport which carries commodities and controlled article and open, inspect, take a sample, and detain or seize; notify the decision within 24 hours.

ሠ) በሃገር መግቢያ እና መውጫ በሮች ላይ የቁጥጥር ሥራዎችን የማከናወን፣

e) Conduct inspection at ports of entry and exit of the country;

ረ) ከእንስሳት ጤናና ደህንነት ጋር በተያያዘ ማንኛውም መረጃ እንዲሰጠው የመጠየቅ፣ የመውሰድ፣

f) Request and obtain any information related to animal health and welfare.

ሥልጣን አለው።

፪/ በንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ (ለ) እና (ሐ) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ባለቤቱ ፈቃደኛ ካልሆነ ከሚመለከተው የሕግ አስከባሪ አካል ጋር በመሆን ተቆጣጣሪው የሳኒተሪ እርምጃ ይወስዳል።

2/ Without prejudice to Sub-Article (1) paragraph (b) and (c) the inspector shall take sanitary measure together with the relevant law enforcing body, when the owner is not cooperative.

፫/ የእንስሳት ጤና ተቆጣጠሪው የተሰጠውን ሥልጣን ያለአግባብ ተጠቅሞ ከተገኘ በወንጀል ሕጉ ተጠያቂ ይሆናል።

3/ The Animal health inspector shall be liable according to the Criminal Code if he abuses his power.

ክፍል አስር
ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

PART TEN
MISCELLANEOUS PROVISIONS

፴፭. ስለቅሬታ አቀራረብና አፈታት

35. Submission and Resolution of Complaint

፩/ በተሰጠው አገልግሎት ላይ ቅር የተሰኘ ተገልጋይ ቅሬታውን ወይም አቤቱታውን ለሚኒስቴሩ ወይም ለባለስልጣኑ ወይም ለክልል እንስሳት ጤና ተቋም ማቅረብ ይችላል።

1/ Any client who feels aggrieved by the service may lodge his complaint to the Ministry, the Authority or the Regional Veterinary Body.

፪/ ሚኒስቴሩ ወይም በባለስልጣኑ ወይም የክልል እንስሳት ጤና ተቋም ጉዳዩን አጣርቶ የውሳኔ ሀሳብ የሚያቀርብ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በፌደራል አስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፹፫/፪ሺ፲፪ መሠረት ያቋቁማል።

2/ The Ministry or the Authority or Regional Veterinary Body shall establish an grievance handling committee according to the Federal Administrative Procedure Proclamation No.1183/2020 to investigate and report on the grounds of the complaint.

፫/ ቅሬታ የቀረበበትን ውሳኔ የሰጠ አካል እና ቅሬታ አቅራቢው በንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የቀረበ አቤቱታ ሲደመጥ በአካል በመገኘት ወይም በሕጋዊ ወኪሎቻቸው አማካኝነት ቀርበው ጉዳዩ እንዲታይ ይደረጋል።

3/ When an appeal filed pursuant to Sub-Article (2) is heard, the Authority that made the contested decision and the appellant shall appear in person or through their legal representatives to have the matter reviewed.

Scanned with MOBILE SCANNER

፬/ እንደ አግባቡ የሚኒስቴሩ ወይም የባለስልጣኑ ወይም የክልሉ እንስሳት ጤና ተቋም ኃላፊ ተጣርቶ የቀረበለትን ሪፖርትና ተያያዥ መረጃዎችን በመመልከት ውሳኔውን ያፀናል፣ ያሻሬል ወይም ማሻሻያ ያደርጋል።

፭/ በዚህ አዋጅ መሠረት ቅሬታ የቀረበበት ውሳኔ ቅሬታው ተመርምሮ እስኪወሰን ድረስ አይፈፀምም። ሆኖም የውሳኔው ሳይፈፀም መቆየት በሕዝብ ላይ የማይመለስ ጉዳት የሚያስከትል ከሆነ የአስተዳደር ተቋሙ የበላይ ኃላፊ ውሳኔው እንዲፈጸም ሊያዝ ይችላል።

፮/ በንዑስ አንቀጽ (፬) የተሰጠ ውሳኔ ላይ ቅር የተሰኘ ቅሬታ አቅራቢ ክለሳ እንዲደረግለት ጉዳዩን ወደ መደበኛ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል።

4/ Higher Official of the Ministry or the Authority or the Head of the Regional Veterinary Body as appropriate shall affirm, set aside or amend the decision after considering the report and other related documents from the appeal committee.

5/ The decision with a complaint under this Proclamation shall not be enforced until the complaint has been investigated and decided. However, if suspension of enforcement of the decision could cause irreversible public damage, the higher official may order the decision to be enforced.

6/ A complainant who is aggrieved on the decision given according to Sub-Article (4) may take the case to a regular court for review.

፴፮. የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም ሰው ይህን አዋጅና አዋጁን ለማስፈፀም የሚወጡ ደንብና መመሪያዎችን ተግባራዊ ለማድረግ መተባበር ይኖርበታል።

36. Obligation to Cooperate

Any person shall have a duty to cooperate for the implementation of this Proclamation, Regulation, and Directives issued pursuant to this Proclamation.

፴፯. የአገልግሎት ክፍያ ስለመሰብሰብ

ሚኒስቴሩ ወይም ባለስልጣኑ ለሚሰጠው አገልግሎት በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ መሠረት የአገልግሎት ክፍያ ይሰበስባል።

37. Collection of Service Fee

The Ministry or the Authority may collect fees for the services rendered in accordance with the Regulation to be issued by the Council of Ministers.

፴፰. ሚስጥር ስለመጠበቅ

ማንኛውም የእንስሳት ጤና ባለሞያ በሚከተሉት ሁኔታዎች ካልሆነ በስተቀር በሥራ አጋጣሚ ከሙርት ጋር የተያያዘ መረጃን ለማንም አሳልፎ መስጠት አይችልም። ሆኖም ግን፦

፩/ ይህን አዋጅ እና አዋጁን ተከትሎ የሚወጣ ደንብን ለማስፈፀም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፣

፪/ ይህን አዋጅ እና አዋጁን ተከትሎ የሚወጣ ደንብን መሠረት አድርጎ ለተመሠረተ የሕግ ሂደት ሲባል፣

፫/ ሚስጥሩ ሊጠበቅለት የሚገባው ሰው በግልፅ ፈቃድ ከሰጠ፣

፬/ ሥልጣን በተሰጠው ፍርድ ቤት ሲጠየቅ፣

38. Confidentiality

No Animal health professional shall disclose any information related to commodity which he acquires in the discharge of his duty, except under the following conditions:

1/ when it is necessary for the application of this Proclamation or any Regulation pursuant to it;

2/ for the purpose of any legal proceedings under this Proclamation or Regulations pursuant to it;

3/ when the concerned person gives his express consent;

4/ when requested to do so by a competent court;

Scanned with MOBILE SCANNER

ሸ/ ለህብረተሰቡ ጥቅም ሲባል ሚኒስቴሩ፣ ባለስልጣኑ ወይም የክልሉ የእንስሳት ጤና ተቋም መረጃው እንዲገለፅ ሲወስን፣ ወይም

ቀ/ የመገናኛ ብዙሃን እና የመረጃ ነፃነትን የሚመለከት ሕግ በሚፈቅደው መሠረት፣ መረጃውን መስጠት ይቻላል።

፴፱. ስለአስተዳደራዊ እርምጃና ቅጣት

፩/ ይህን አዋጅ ወይም አዋጁን ለማስፈፀም በሚኒስትሮች ም/ቤት በሚወጣ ደንብና በሚኒስቴሩ የሚወጡ መመሪያዎችን ያላሟሉ ምርቶች በጊዜያዊነት ሊዘገዩ፣ ሊያዙ፣ ሊወረሱ ወይም ተመልሰው ሊሰበሰቡ ወይም ተያያዥ ሕጋዊ እርምጃዎች ሊወሰድባቸው ይችላል።

፪/ ሚኒስቴሩ ወይም ባለስልጣኑ ወይም የክልል ጤና ተቋም በዚህ አዋጅ እና አዋጁን ተከትሎ የሚወጣ ደንብና መመሪያን የተላለፈ ማንኛውም ሰው ላይ አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል። ዝርዝሩ በሚኒስቴር መ/ቤቱ በሚወጣው መመሪያ ይወሰናል።

፫/ ማንኛውም ሰው ፡-

ሀ) ሆን ብሎ በበሽታ አስተላላፊ፣ በበሽታ አምጪ ተህዋስ፣ በመርዝ እንደ አግባቡ የተያዘ ወይም የተበከለ ምርት ወይም ቁጥጥር የሚደረግበት ቁስን የያዘ፣ ያመረተ፣ የሸጠ፣ ለሽያጭ ያቀረበ፣ ያንዝዘና ያከፋፈለ፣ እንደሆነ ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራትና ከብር ፲ ሺህ (አስር ሺህ ብር) በማያንስ ከብር ፳፭ ሺህ (ሃያ አምስት ሺህ ብር) በማይበልጥ የገንዘብ መቀጫ ይቀጣል።

ለ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፮ ንዑስ አንቀፅ (፩) መሠረት የእንስሳውን በሽታ ሆን ብሎ ያላሳወቀ እንደሆነ የደረሰውን ጉዳት ግምት ውስጥ በማስገባት ከአንድ ዓመት በማይበልጥ እስራት ወይም ከብር ፫ ሺህ (ሶስት ሺህ ብር) በማይበልጥ የገንዘብ መቀጫ ይቀጣል። ሆኖም ግን ጥፋቱን የፈፀመው የእንስሳት ጤና ባለሞያ ወይም ድርጅት ከሆነ ከሁለት ዓመት በማይበልጥ እስራት እና ከብር ፲ ሺህ (አስር ሺህ ብር) በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል።

5/ where the Ministry, the Authority or Regional Veterinary Body, authorizes the disclosure for the sake of public interest;

6/ Disclosure of information shall be permitted in accordance with the applicable law on media freedom and access to information.

39. Administrative Measure and Penalty

1/ Commodities that do not comply with this Proclamation, Regulation issued by the Council of Ministers, or Directives issued by the Ministry may be temporarily delayed, seized, confiscated, or recalled, and subject to related legal actions.

2/ The Ministry, the Authority, or the Regional Veterinary Body shall take administrative measures against any person who violates this Proclamation, and Regulations and Directives issued pursuant to it. The details shall be determined by Directives issued by the Ministry.

3/ Any person who:

a) intentionally posses, manufactures, sells, offers for sell, transports, or distributes in any manner; commodity, or controlled article knowing that it is infected with or contaminated by an animal disease agent, infectious organism, toxin, or is punishable up on rigorous imprisonment not exceeding five years and a fine not less than 10000 Birr and not exceeding 25000 Birr.

b) Intentionally fails to report notifiable animal disease according to Sub-Article (1) Article 6 of this Proclamation, taking the damage caused into consideration, shall be punishable with simple imprisonment not more than one year or fine not exceeding 3000 Birr. However, if the offence is committed by animal health professional or institution shall be punishable with simple imprisonment not more than two years and fine not exceeding 10000 Birr.

Scanned with MOBILE SCANNER

ሐ) በዚህ ረቂቅ አዋጅ በአንቀጽ ፰ ንዑስ አንቀፅ (፩) መሠረት የእንስሳት በሽታ ከገባበት አካባቢ ምርት፣ በበሽታ አስተላላፊ ተህዋስ የተያዘ ወይም የተበከለ ቁስን ወደ ሌላ ሥፍራ ያለፈቃድ ያንቀሳቀሰ ፣ እንደሆነ ከሶስት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት እና ብር ፲፭ ሺህ (አስራ አምስት ሺህ ብር) በማይበልጥ የገንዘብ መቀጫ ይቀጣል።

c) Moves commodities, infected or contaminated articles from an infected area to other place without permission, according to Article 8 Sub-Article (1) shall be punishable with simple imprisonment not more than three years or a fine not exceeding 15,000 Birr.

መ) በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፰ ንዑስ አንቀፅ (፬) መሠረት ሪፖርት መደረግ ባለበት ወይም በአዲስ ወይም እንደገና በተከሰተ በሽታ የተያዘ ወይም መያዙ የተጠረጠረ እንስሳን ከሌሎች ለይቶና አግልሎ እንዲያቆይ በባለሙያ ተነግሮት ለይቶና አግልሎ ያላቆየ እንደሆነ ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ወይም ከብር ፫ ሺህ (ሶስት ሺህ ብር) በማይበልጥ የገንዘብ መቀጫ ይቀጣል።

d) Fails to confine and isolate an animal which is infected or suspected to be infected with a notifiable or emerging and re-emerging animal disease from other animals according to Article 8 Sub-Article (4) as advised by professional, shall be punishable with simple imprisonment not more than one year or a fine not exceeding 3000 Birr.

ሠ) በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፲፫ ንዑስ አንቀፅ (፩) መሠረት እንስሳትን ያለ ጉዞ ፈቃድ ያዘዋወረ እንደሆነ ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራትና ከብር ፲፭ ሺህ (አስራ አምስት ሺህ ብር) በማይበልጥ የገንዘብ መቀጫ ይቀጣል።

e) Moves animal without movement permit according to Article 13 Sub-Article (1) is punishable by rigorous imprisonment not exceeding one year and a fine not exceeding 15,000 Birr.

ረ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፫ መሠረት እንስሳትን ያለ ፈቃድ የሰበሰበና ያሳሳወቀ እንደሆነ ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ወይም ከብር ፫ ሺህ (ሶስት ሺህ ብር) በማይበልጥ የገንዘብ መቀጫ ይቀጣል።

f) Holds animal gathering without permission according to Article 13, is punishable up onsimple imprisonment not more than one year or fine not exceeding 3000 Birr.

ሰ) በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፲፮ መሠረት ከባለስልጣኑ ፈቃድ ሳያገኝ ምርትን ወይም ቁጥጥር የሚደረግባቸው ቁሶችን ወደ ሃገር ውስጥ ያስገባ ወይም በሃገሪቱ ድንበር ውስጥ ያሸጋገረ እንደሆነ ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት እና ከብር ፶ሺህ (ሃምሳ ሺህ ብር) በማይበልጥ የገንዘብ መቀጫ ይቀጣል።

g) Imports or transit commodity or controlled article without permission from the authority according to Article 16 is punishable by rigorous imprisonment of not more than five years and a fine not exceeding 50,000 Birr.

ሸ) በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፲፰ መሠረት ዓለምአቀፍ የእንስሳት ጤና ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሳያገኝ ምርት ወይም ቁጥጥር የሚደረግባቸው ቁሶችን ወደ ውጪ የላከ እንደሆነ ከአምስት ዓመት

h) exports a commodity or controlled article without being issued an international veterinary certificate according to Article 18 is punishable by rigorous imprisonment of not more

Scanned with MOBILE SCANNER

በማይበልጥ ጽኑ እስራትና ከብር ፱ ሺህ (ሃምሳ ሺህ ብር) በማይበልጥ የገንዘብ መቀጫ ይቀጣል።

than five years and a fine not exceeding 50,000 Birrs.

ቀ) በአንቀጽ ፳፩ መሠረት ፈቃድ ሳያገኝ ቄራ ወይም ማቀነባበሪያ ደርጅት ያቋቋመና አገልግሎት የሰጠ እንደሆነ ከአምስት ዓመት ባልበለጠ ጽኑ እስራትና ከብር ፩፻፶ ሺህ (አንድ መቶ ሃምሳ ሺህ ብር) በማይበልጥ የገንዘብ መቀጫ ይቀጣል።

i) Establishes an abattoir or animal product processing facility and gives service without permission according to Article 21 is punishable by rigorous imprisonment of not more than five years and a fine not exceeding 150,000 Birr.

በ) በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፳፫ መሠረት የእንስሳት ውጤቶችን ከጣዕድ ነገር ጋር የከለሰ፣ እና ለገበያ ያቀረበ እንደሆነ ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት እና ከብር ፶ ሺህ ብር (ሃምሳ ሺህ ብር) በማይበልጥ የገንዘብ መቀጫ ይቀጣል

j) Adulterates animal products with foreign substances and offers them for sale Pursuant to Article 23 of this Proclamation shall be punishable by rigorous imprisonment not exceeding five years and a fine not exceeding 50,000 (Fifty Thousand) Birr.

ተ) በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፳፫ መሠረት የደህንነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያልተሰጠውን ምርቶችንና ተረፈ-ምርቶችን ለገበያ ያቀረበ እንደሆነ ከሶስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት እና ከብር ፲፭ ሺህ (አስራ አምስት ሺህ ብር) በማይበልጥ የገንዘብ መቀጫ ይቀጣል።

k) Offer for sale commodities without a safety assurance certificate pursuant to Article 23 of this Proclamation shall be punished with rigorous imprisonment not exceeding three years and a fine not exceeding 15,000 Birr.

ቸ) በአንቀጽ ፳፮ መሠረት ከሚኒስቴሩ ወይም ከሚመለከተው አካል ፈቃድ ሳያገኝ በእንስሳት ላይ ሙከራና ምርምር ያካሄደ እንደሆነ ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራትና ከብር ፲ ሺህ (አስር ሺህ ብር) በማይበልጥ የገንዘብ መቀጫ ይቀጣል።

l) performs experiments or conducts research on animals without permission from the Ministry or other competent Authority according to Article 26 is punishable by rigorous imprisonment of not more than five years and a fine not exceeding 10,000 Birr.

ነ) በአንቀጽ ፳፱ ከሚኒስቴሩ ወይም ከሚመለከተው አካል ፈቃድ ሳያገኝ በመካነ እንስሳት ወይም ለሰርከስ ወይም በጊዜያዊነትም ሆነ በቋሚነት እንስሳትን አግልሎ በአንድ ሥፍራ ማስቀመጫ ያቋቋመ እንደሆነ ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ወይም ከብር ፲ ሺህ (አስር ሺህ ብር) በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል።

m) Establishes a zoo or circus or any other permanent or temporary facility for the confinement of animals without permission from the Ministry or other competent Authority according to Article 29 is punishable by simple imprisonment not more than one year or a fine not exceeding 10000 Birr.

Scanned with MOBILE SCANNER

ነ) በአንቀጽ ፴፩ መሠረት ያለባለቤቱ ጥበቃ በመንገድ ላይ መውጣቱ የተጠረጠረ እንስሳ ባለቤት ይህንኑ ሪፖርት ያላደረገ እንደሆነ ከስድስት ወር በማይበልጥ ቀላል እስራት ወይም ከብር ፩ ሺህ (አንድ ሺህ ብር) በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፤

n) The holder of stray animal fails to report stray animal according to Article 30 is punishable by simple imprisonment not more than six months or a fine not exceeding 1000 Birr.

ኘ) በዚህ አዋጅ መሠረት በሚኒስቴሩ ወይም በባለስልጣኑ ወይም በክልሉ የእንስሳት ጤና ባለሞያ ወይም በሙል ተቀባይ የእንስሳት ጤና ባለሙያ የተወሰደን ናሙና ያበላሸ እንደሆነ ከሁለት ዓመት ባልበለጠ ቀላል እስራትና ከብር ፫ ሺህ (ሦስት ሺህ ብር) ባልበለጠ የገንዘብ መቀጫ ይቀጣል፤፤

o) Cause damage to any samples taken by the Ministry or the Authority or Regional Animal Health Officer or assignee is punishable up on simple imprisonment not more than two years and fine not exceeding 3000 Birr.

አ) ማንኛውንም በሽታ አስተላላፊ፣ የበሽታ አምጪ ተህዋስ፣ መርዝ ወይም ሌላ ጎጂና በካይ ነገርን ሆን ብሎ ወደ ሃገሪቷ እንዲገባ የፈቀደ ወይም እንዲገባ ያደረገ እንደሆነ ከ ፭ ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራትና ከብር ፶ ሺህ (ሃምሳ ሺህ ብር) በማይበልጥ የገንዘብ መቀጫ ይቀጣል፤፤

p) Intentionally permits or cause the introduction in to the country or the spread of any animal disease agent, infectious organism, toxin or harmful contaminant is punishable up on rigorous imprisonment not more than five years and fine not exceeding 50,000 Birr.

ከ) ዓለም አቀፍ የእንስሳት ጤና ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጠውን ምርት ጥራት እና ደህንነት እንዲጠበቅ ያላደረገ እንደሆነ ከሶስት ዓመት ባልበለጠ ቀላል እስራት እና እስከ ብር ፳፭ ሺህ (ሃያ አምስት ሺህ ብር) በሚደርስ የገንዘብ መቀጫ ይቀጣል፤፤

q) Failure to maintain the quality and safety of the commodity for which an international veterinary certificate has been issued is punishable up on simple imprisonment not more than three years and a fine of up to 25,000 Birr (Twenty-Five Thousand Birr).

ኸ) ያለ እንስሳት ጤና ባለሞያ ፈቃድ ሳኒተሪ እርምጃ የተወሰደበት ምርት የያዘ ወይም የታሸገ መያዣን ወይም ምልክቱን የሰበረ ወይም የከፈተ እንደሆነ ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ወይም ከብር ፲ ሺህ (አስር ሺህ ብር) በማይበልጥ የገንዘብ መቀጫ ይቀጣል፤፤

r) Without the authorization of an animal health professional, posses commedity that have been subjected to sanitary measures, or opens, or breaks the seal of a container, shall be punishable by simple imprisonment for a period not exceeding one year, or a fine not exceeding 10,000 (Ten Thousand) Birr.

ወ) ከሚኒስቴሩ እውቅና እና ፈቃድ ውጪ ሪፖርት መደረግ ያለበት በሽታ ወይም በሽታ አምጪ ተህዋስ መከሰቱን በህትመት ውጤቶች ወይም በብዙሃን መገናኛ ላይ እንዲወጣ የሰጠ እንደሆነ በሁለት ዓመት ጽኑ እስራትና ከብር ፲ ሺህ (አስር ሺህ ብር) ባልበለጠ የገንዘብ መቀጫ ይቀጣል፤፤

s) Submits any document for publication or mass media referring to the occurrence of a notifiable animal disease agent or infectious organism in the country without prior permission from the Ministry or other relevant bodies is punishable by rigorous imprisonment not more than two years and fine not exceeding 10,000 Birrs.

Scanned with MOBILE SCANNER

ሀ) በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል በወንጀል ሕግ አንቀፅ ፴፬ በተመለከተው መሠረት በዚህ አዋጅ በተመለከቱ ጥፋቶች ተካፋይ በሚሆንበት ጊዜ በወንጀል ሕጉ አንቀፅ ፺ መሠረት ይቀጣል።

t) Juridical person who participates in the commission of offenses under this Proclamation as provided in Article 34 of the Criminal Code shall be punishable in accordance with Article 90 of the Code.

፬/ ማንኛውም የእንስሳት ጤና ባለሞያ በአዋጁ አንቀፅ ፴፰ መሠረት ካልሆነ በስተቀር በሥራ አጋጣሚ ያገኘውን በሚስጥር መጠበቅ ያለበት መረጃን አሳልፎ የሰጠ እንደሆነ ከሶስት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ወይም ብር ፲ ሺህ (አስር ሺህ ብር) የገንዘብ መቀጫ ይቀጣል።

4/ Any animal health profeesional who discloses confidential information acquired in the course of performing his official duty except for in conditions listed down in Article 38 shall be punishable by simple imprisonment of not more than three years or a fine not exceeding 10,000 Birrs.

፵. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል።

፪/ ሚኒስቴሩ ይህን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የወጡ ደንቦችን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

40. Power to Issue Regulations and Directives

1/ The Council of Ministers may issue Regulations necessary for the implementation of this Proclamation.

2/ The Ministry may issue Directives necessary for the implementation of this Proclamation and Regulations issued pursuant to Sub-Article (1) of this Article.

፵፩. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

በስራ ላይ ያሉ ደንቦችና መመሪያዎች ከዚህ አዋጅ ጋር እስካልተቃረኑና በሌሎች ደንቦችና መመሪያዎች እስካልተተኩ ድረስ ተፈፃሚነታቸው ይቀጥላል።

41. Transitory Provisions

Exsting Regulations and Directives shall remain functional as long as they do not contradict this Proclamation and unless they are not replaced with other Regulations and Directives.

፵፪. የተሻሩና ተፈፃሚነት የሌላቸው ሕጎች

፩/ የእንስሳት በሽታዎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ ቁጥር ፪፻፷፯/፪ሺ፬፻፺፭ እና የስጋ ምርመራ አዋጅ ቁጥር ፪፻፸፬/፩ሺ፱፻፸፪ እንደተሻሻለ በዚህ አዋጅ ተሽረዋል።

1/ Animal Disease Prevention and Control Proclamation No. 267/2002 and Meat Inspection proclamation No. 274/1970 (as amended) is hereby repealed.

፪/ ይህን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም ሕግ በዚህ አዋጅ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

2/ Any law which is inconsistent with this Proclamation shall have no effect with respect to matters governed by this Proclamation.

Scanned with MOBILE SCANNER

፵፫. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ነሐሴ ፮ ቀን ፪ሺ፯፱ ዓ.ም

ታዬ አጽቀሥላሴ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

43. Effective Date

This Proclamation shall come into effect on the date of its publication in the Federal Negarit Gazettee.

Done at Addis Ababa,on this 12th day of August, 2025.

TAYE ATSIKESELASSE

PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

Scanned with MOBILE SCANNER